# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ 84ኛ ዓመት ቁጥር 010 መስከረም 10 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# "የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናን የትርምስ ማዕከል ለማድረግ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሊቆም ይገባል"

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናን የትርምስ ማዕከል ለማድረግ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሊቆም ይገባል ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነብያት ጌታቸው በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ዙሪያ ትናንት ሳምንታዊ መግለጫ ሰጥተዋል።

አምባሳደሩ በመግለጫቸው፤ ኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ ለጎረቤት ሀገራት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ፣ የሰከነ እና መርሕን መሠረት ባደረገ በበጎ መንፈስ የተቃኘ ዘላቂ ዲፕሎማሲ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በየጊዜው ለሚሰነዘሩ ትንኮሳዎች ምላሽ የመስጠት ሂደት ውስጥ አትገባም፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናን የትርምስ ማዕከል ለማድረግ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሊቆም ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ከቅርብ ጎረቤቶቿ ጋር የሚደረጉ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን በቅርበት እንደምትከታተልና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜም ተገቢውን ምላሽ እንደምትሰጥም ገልፀዋል።

በሳምንቱ ከአውሮፓ ኅብረት፣ ከአሜሪካ እና ከተመድ ልዩ መልዕክተኞች ጋር ውይይቶች መካሄዳቸውን ያነሱት አምባሳደር ነብያት፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴ ለሁሉም መልዕክተኞች ኢትዮጵያ የአፍሪካ ቀንድ ሠላምና መረጋጋት የሰፈነበት ሆኖ የኢኮኖሚ ሽግግር እንዲኖር ለማድረግ የምታደርገውን ጥረት አስረድተዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከመስከረም 14 እስከ 20/2017 ዓ.ም በሚካሄደው 79ኛው የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ በንቃት

"የአፍሪካ ቀንድ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር ነብያት ጌታቸው

# በምርኩዝ መራመድ መቄዶንያን ከመርዳት ያልገታቸው አርበኞች

**ሔርሞን ፍቃዱ**

መቄዶንያ ሲባል ቀድሞ የሚመጣልን ‹‹ሰው ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው›› የሚል የማኅበሩ ቁልፍ ሐረግ ነው፡፡ ማዕከሉ ለረጅም ዓመታት ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን አረጋውያንን፣ የአዕምሮ ሕመምተኞችንና ሌሎች ወገኖችን ከያሉበት በማንሳት መጠለያና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህን በጎ ተግባር ለመደገፍ የጥንታዊት ኢትዮጵያ

በምርኩዝ መራመድ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# "በቀጣናው ያሉትን የቱሪዝም ሀብቶች በትብብር በማልማት ለተተኪው ትውልድ ማሻገር ይገባል"

- ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር)
የኢጋድ ዋና ጸሐፊ

ገጽ 6

# የሠላማዊ ትግል ፋናወጊው ሕይወት

**ፋንታነሽ ክንዴ**

የሠላማዊ ትግል ፋናወጊው እና ተምሳሌቱ በየነ ጴጥሮስ (ፐ/ር) ሥርዓተ ቀብራቸው ትናንትና ተፈጽሟል።

ፐሮፌሰሩ በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ለብዙዎች የዕውቀት አባት፣ በአመራርነት ደግሞ ቅን አገልጋይ መሆናቸው ይወሳል፡፡ በፖለቲካ ተሳትፏቸው የሠላማዊ ትግል ተምሳሌት በመሆንም አብዝተው ይታወቃሉ። ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ብለው ባሰቡበት ቦታ ሁሉ ቀድመው መገኘት መገለጫቸው ነው ይሏቸዋል በቅርበት የሚያውቋቸው፡፡

በየነ ጴጥሮስ (ፐ/ር) በአሁኑ አጠራር በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሃዲያ ዞን በመጋቢት ወር 1942 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ምሥራቅ ባደዋቾ በሾኔ፣ በኩየራ፣ በአዳማ የተከታተሉ ሲሆን፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርትን ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በአሜሪካን ሀገር ተከታትለዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነ ሕይወት የትምህርት ዘርፍ በመምህርነትና በተመራማሪነት ለበርካታ ዓመታት

የሠላማዊ ትግል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





ፎቶ፡- በሪሁን ታደሰ






የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ስለሺ ግርማ

# ሚኒስቴሩ ከበዓላት ጋር የተያያዙ የጉብኝት ጥቅሎች መዘጋጀታቸውን አሳወቀ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በመስከረም ወር የሚከበሩ የአደባባይ በዓላትን መሠረት ያደረጉ የጉብኝት ጥቅሎች (ፓኬጆች) መዘጋጀታቸውን ቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ስለሺ ግርማ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመስከረም ወር ቀጣይ ቀናት መስቀል፣ ኢሬቻ እና የዓለም ቱሪዝም ቀን እንዲሁም የተለያዩ አካባቢዎች የዘመን መለወጫ በዓላት ይከበራሉ።

ሚኒስቴሩም በወሩ የሚከናወኑ የተለያዩ በዓላት ለቱሪዝም ገቢ ዕድገት ያላቸውን ሰፊ ጠቀሜታ በመረዳትና ከክልሎች ጋር በመነጋገር የተለያዩ የጉብኝት ጥቅሎችን አዘጋጅቶ እያስተዋወቀ ይገኛል ብለዋል።

በደቡብ የሀገሪቷ ክፍል ያሉ አንዳንድ አካባቢዎች የዘመን መለወጫ በዓላትን በመስከረም ወር እንደሚያከብሩ አመላክተው፤ በዓላትን ምክንያት በማድረግ የተለያዩ እንግዶች ከነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክና ከጫሞ ሐይቅ ጋር የተያያዙ የጉብኝት መርሐግብሮች ላይ እንዲሳተፉ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በየአካባቢው የሚገኙ ሌሎች የቱሪስት መስሕቦችን በመለየት የማስተዋወቅና የገቢ ምንጭ ለማድረግ ተቋሙ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቁመዋል።

በዓላቱ በሚከበሩበት ወቅት በአዲስ አበባና በተለያዩ የክልል ከተሞች የሚገኙ፤ በዩኔስኮ የተመዘገቡና አዲስ የለሙ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ዜጎች በልዩ ሁኔታ ለማስጎብኘት ዝግጅት መደረጉን አንስተዋል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የቱሪስት ቁጥር የምታስተናግድባቸው ወቅቶች የዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ናቸው ያሉት ሚኒስቴር ዴኤታው፤ በተያዘው ወር የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሀገሪቷን የሚጎበኙበት ወቅት በመሆኑ በርካታ ገቢ ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅበት ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የመስቀል ደመራና የኢሬቻ በዓላት ሲከበሩ በርካታ ሚሊዮን ሕዝቦች አደባባይ ወጥተው በአብሮነት፣ በፍቅርና በአንድነት የሚያከብሯቸው በዓላት ከመሆናቸው ባሻገር ከመላው ዓለም የሚመጡ ቱሪስቶች የሚታደሙባቸው ደማቅ ሥነሥርዓቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

አቶ ስለሺ እንደተናገሩት፤ በዓላቱ ሃይማኖታዊ እንዲሁም ባሕላዊ ትውፊት የሚፈጸሙባቸውን ሁነቶች ይዘዋል። ከሃይማኖታዊና ባሕላዊው ሥርዓታቸው ባለፈም ኢኮኖሚውን የማነቃቃት ሚናቸው የጎላ ነው።

የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ለመጨመር እንግዶች በሚሄዱበት አካባቢ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ ለሆቴል አሠሪና ሠራተኞች፣ ለአስጎብኚዎችና ለተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎች ሥልጠና መሰጠቱን ተናግረዋል፡፡


ሥልጠናው ቀጣይነት ያለው ምቹ አገልግሎቶችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገራት ጎብኚዎች በማቅረብ የቱሪዝም ገቢውን ለማሳደግ ያለመ መሆኑን አንስተዋል።

በተጠናከረ ሁኔታ የሀገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲያድግ ታሳቢ ተደርጎ እየተሠራ መሆኑ ሚኒስቴር ዴኤታው ገልጸዋል።

ዜጎች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢ የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ቅርሶችን እንዲጎበኙ እንዲሁም ባሕላዊ፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ሁነቶች ላይ የተመሠረቱ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ አቶ ስለሺ ግርማ ጥሪ አቅርበዋል።

# በመዲናዋ ከቱሪዝም ዘርፍ ከ119 ቢሊዮን ብር በላይ ወደኢኮኖሚው ፈሰስ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ማሕሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በ2017 በጀት ዓመት ከቱሪዝም ዘርፍ ከ119 ቢሊዮን በላይ ብር ወደ ከተማው ኢኮኖሚ ፈሰስ ለማድረግ መታቀዱን የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ሳምሶም አይናቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2017 ከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻ በማድረግ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ቱሪስቶች 119 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወደከተማው ኢኮኖሚ ፈሰስ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

የ2017 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ ባለፈው ዓመት የነበሩ ጥንካሬ እና ድክመቶችን በመለየት የተሻለ አፈጻጸም ላይ ለመድረስ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ከዘጠኝ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 55 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ለማድረግ የታቀደ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ቁጥርን አንድ ሚሊዮን በማድረስ 64 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ከተማዋ ኢኮኖሚ ላይ ፈሰስ ለማድረግ ታቅዶ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በአጠቃላይ በ2017 በጀት ዓመት ከ10 ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች 119 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ለማድረግ ታቅዷል ብለዋል፡፡

ከጎብኚዎች ፈሰስ የሚደረገው ገንዘብ የሚሰላው በጉብኝት መግቢያ፣ በአስጎብኚ ማኅበራት ገቢ፣ ለትራንስፖርት እና ሆቴል አገልግሎቶች በሚከፈል ክፍያ እንዲሁም በሌሎች የቱሪዝም ተዋናዮች በሚገኝ ገቢ መሆኑን አቶ ሳምሶም አስረድተዋል፡፡

ወደ ከተማዋ የሚመጡ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ባዛር እና ለሃይማኖታዊ በዓላት ለመታደም፣ የሕክምና እና የሥልጠና አገልግሎት ለማግኘት፣ እንዲሁም ለጉብኝትና ሰው ጥየቃ ዓላማ የሚመጡትንም የሚያጠቃልል መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

የከተማዋን የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስት ቁጥር ለማሳደግ በመዲናዋ የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን ቁጥር የማሳደግ፣ ነባር መዳረሻዎች ላይ ዕሴት የመጨመር፣ ሳቢ እና ምቹ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራዎች እንደሚሠሩም ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም ከተማዋን ብሎም መዳረሻዎችን የተለያዩ አማራጮች በመጠቀም ለዓለም የማስተዋወቅና ተደራሽነታቸውን የማሳደግ ሥራ እንደሚሠራም አቶ ሳምሶም አስታውቀዋል፡፡

በከተማዋ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት በተለይም በመስከረም ወር ላይ የሚከበረው የመስቀል እና ኢሬቻ በዓላት ከተማዋን በማስተዋወቅ መዳረሻ ከማድረግ በተጨማሪም ገጽታ በመገንባት ከሀገር ውስጥ ሁነቶች በተጨማሪ ዓለም አቀፍ ኩነቶች ወደ ከተማዋ እንዲመጡ የሚያስችል መሆኑን አያይዘው ተናግረዋል

በዚህም በመስከረም ወር የሚከበሩትን የመስቀል እና የኢሬቻ በዓላት ለሀገር ውስጥ እና የውጭ ጎብኚዎችን ለማስተናገድ የተለያዩ ሁነቶችን ከማዘጋጀት ጀምሮ የተለያዩ ዝግጅቶች እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# ለቴሌኮምና ዲጂታል መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ መመደቡን ኢትዮቴሌኮም አስታወቀ

## - ገቢውንም 163 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ለማድረስ አቅዷል

**ማርቆስ በላይ**



ወ/ሪት ፍሬሕይወት ታምሩ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮቴሌኮም በ2017 በጀት ዓመት የቴሌኮምና ዲጂታል መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ዶላር መመደቡን አስታወቀ፡፡ ገቢውን 163 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር፣ የደንበኞቹን ቁጥር 83 ሚሊዮን ለማድረስ ማቀዱም ተገልጿል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ ኢትዮቴሌኮም በ2017 በጀት ዓመት የቴሌኮምና ዲጂታል መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ መመደቡን ተናግረዋል፡፡

የዲጂታል ኢትዮጵያና የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ አስተማማኝ በሆነ የቴሌኮምና ዲጂታል መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ይደረጋል ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ እነዚህን ማስፋፊያዎች ተግባራዊ ለማድረግ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ዶላር ተመድቧል ብለዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ የደንበኞችን ብዛት 83 ሚሊዮን ለማድረስ መታቀዱን ጠቅሰው፤ የሞባይል ደንበኞችን ቁጥር 79 ነጥብ 7 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዷል ብለዋል፡፡

የሞባይል ዳታና ኢንተርኔት ተጠቃሚዎችን 47 ነጥብ 4 ሚሊዮን፣ የፊክስድ ብሮድባንድ ደንበኞችን 934 ሺህ ለማድረስ ታቅዷል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

የቴሌብር አገልግሎት በስፋት ተደራሽ በማድረግ የደንበኞችን ቁጥር 55 ሚሊዮን ለማድረስ እንደታቀደ በመግለጽ፤ የወኪሎችን ቁጥር 275 ሺህ፣ ግብይት የሚፈጽሙ ነጋዴዎችንም 367 ሺህ ለማድረስ ታቅዷል ብለዋል፡፡

የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ ዓለም አቀፍ ስትራቴጂያዊ አጋርነትን በማስፋት፣ ተወዳዳሪ አገልግሎት በማቅረብ፣ የረሚታንስ አገልግሎት ለማሻሻል እንደታቀደ ጠቅሰው፤ በበጀት ዓመቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት መጠኑን ወደ 282 ነጥብ 85 ሚሊዮን ዶላር ለማሳደግ መታቀዱን ገልጸዋል፡፡

የቴሌኮም መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት አንድ ሺህ 298 አዲስ የሞባይል ጣቢያዎችን ለመገንባት መታቀዱን የገለጹት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ የ4ጂ አገልግሎት በ500 ተጨማሪ ከተሞችና የ5ጂ አገልግሎት በ15 ተጨማሪ ከተሞችን ተደራሽ ለማድረግ ታቅዷል ብለዋል፡፡

አቅርቦትን ከማረጋገጥ አንጻር ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ የቴሌኮም መሣሪያዎችን ለግለሰብና ድርጅቶች ለማቅረብ መዘጋጀታቸውንም ጠቁመዋል፡፡

ኩባንያው የቴሌኮምና የዲጂታል መሠረተ ልማቶችን በመጠቀም የደንበኛ እርካታን የሚያሳድጉ ጥራት ያለው አገልግሎቶች ለማቅረብ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ የቴሌኮምና የዲጂታል መሠረተ ልማቶችን በመዘርጋት፣ ለዜጎች፣ ቢዝነሶችና ተቋማት ዘመናዊ ዲጂታል መፍትሔዎች እንደሚያቀርብ ገልጸዋል፡፡

በዲጂታል መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ከመሠረታዊ የቴሌኮም አገልግሎቶች ባሻገር የድርጅት ደንበኞችን አሠራር ሥርዓት የሚያዘምኑ አሠራሮች እንደሚተገበሩ በመግለጽ፤ የመረጃና የጥሪ ማዕከል አገልግሎት፣ የቪዲዮ፣ የጌምና የሙዚቃ አገልግሎቶች፣ የዲጂታል ግብርና፣ ጤናን ጨምሮ ትምህርትና ስማርት ከተማ አቅርቦት ለማሳደግ መዘጋጀታቸውንም አስረድተዋል፡፡

የሰው ሠራሽ አስተውሎት ትግበራ የተጀመሩትን አጠናክሮ መቀጠልና በኔትዎርክ፣ የቴሌኮም ማጭበርበርን ለመከላከል ጥቅም ላይ እንደሚውል ገልጸው፤ የደንበኞችን አገልግሎት ከማሻሻል አንፃር በስፋት ለመጠቀም መታቀዱን ጠቁመዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ የገቢ አማራጮችንና የገቢ መጠን ከማሳደግ በተጨማሪ የኩባንያውን የወጪ ቁጠባ ስትራቴጂ ትግበራን በማጠናከር ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ያህል ወጪን ለመቆጠብ መታቀዱንም ገልጸዋል፡፡

# ለሆራ አርሰዲ የኢሬቻ በዓል አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 ዓ.ም በሆራ አርሰዲ ኢሬቻ በዓል የሚታደሙ እንግዶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ አስፈላጊው ዝግጅት መጠናቀቁን የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የቢሾፍቱ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ገዛኸኝ ደጀኔ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘንድሮ ለሚከበረው የሆራ አርሰዲ ኢሬቻ በዓል አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል፡፡

ለ2017 ዓ.ም በከተማዋ በድምቀት ለሚከበሩት ኢሬቻና የመስቀል በዓል ከሦስት ወራት በፊት ጀምሮ ዝግጅት ሲደረግ ቆይቷል ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ በከተማው እንግዶችን የመቀበል ልምድና ተሞክሮዎች መሠረት በሆራ አርሰዲ በዓል የሚታደሙ እንግዶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ዝግጅት ተጠናቋል ብለዋል፡፡

ለዘንድሮው የሆራ አርሰዲ በዓል አከባበር ዙሪያ ከከተማው ሕዝብ ጋር ውይይት በማድረግ በሁሉም ዘርፎች ላይ አስፈላጊው ዝግጅት መጠናቀቁን ጠቅሰው፤ የከተማው ማኅበረሰብ የኢሬቻና የመስቀል በዓላትን በእንግዳ ተቀባይነት መንፈስ ለማክበር መዘጋጀቱን



አቶ ገዛኸኝ ደጀኔ

ገልጸዋል፡፡

ሆቴሎች ወደ ከተማዋ የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል የሚያስችል ሙሉ ዝግጅት ስለማድረጋቸው ግምገማ መካሄዱን በመግለጽ፤ የሆራ አርሰዲ ክብረበዓል በሠላም እንዲከበር በየደረጃው ካሉ የኀብረተሰብና የፀጥታ መዋቅሮች ጋር ዝግጅት መደረጉንም ተናግረዋል፡፡

በከተማው ሆቴሎችን፣ መኝታ ቤቶችና የመስተንግዶ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንግዶችን ለማስተናገድ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጋቸውን ገልጸው፤ የዋጋ ጭማሪዎች እንዳይደረጉ ከባለሀብቶች ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን በተቋቋመው ግብረኃይል በኩል ቁጥጥር እንደሚደረግም ጠቁመዋል፡፡

በዓመት አንዴ በከተማዋ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል ለቱሪዝም ዘርፉ፣ በኢኮኖሚና በሥራ ዕድል ፈጠራ ዘርፎች ላይ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው የገለጹት ምክትል ከንቲባው፤ የሆራ አርሰዲ በዓል የከተማዋ የገጽታ ግንባታ፣ የገቢ ምንጭ በመሆኑ የማጠናከር ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል የኢሬቻ በዓል አከባበር ላይ የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ድክመቶች ተለይተው መገምገማቸውን ጠቅሰው፤ የዘንድሮው በዓል በተሻለ መልኩ እንግዶችን ለመቀበል ከአመራር እስከ ማኅበረሰቡ ድረስ ዝግጅት መጠናቀቁን ተናግረዋል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ ቢሾፍቱ ከተማን የቱሪስት ማዕከል ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በከተማው ኮሪደር ልማት ጋር ተያይዞ መንገዶችን የማስፋት ከተማን የማስዋብ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡



አቶ ጀማል ዓሊ

## አርሶ አደሩ በድርቅ ወቅት የሚደርስበትን ኪሳራ የመድኅን ዋስትና በመግዛት ሊያካክስ ይገባል

### - የመጀመሪያው ዙር የእንስሳት መድኅን ዋስትና ሽያጭ ተጀመረ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አርሶ አደሩ በድርቅ ወቅት የሚደርስበትን ኪሳራ የእንስሳት መድኅን ዋስትና በመግዛት ሊያካክስ እንደሚገባ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። የመጀመሪያው ዙር የእንስሳት መድኅን ዋስትና ሽያጭ ነሐሴ 26 ቀን 2016 ዓ.ም የጀመረ ሲሆን መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሏል።

በግብርና ሚኒስቴር የአደጋ ቅነሳና አካታች ኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ጀማል አሊይ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ የእንስሳት መድን ዋስትና አርብቶ አደሩ በድርቅ ምክንያት እንስሳቱን እንዳያጣ አስቀድሞ አካባቢዎቹ በሳተላይት ከተለዩ በኋላ በአንድ ወር ውስጥ ውሃ፣ ሣር እና መድኃኒትን ለእንስሳት ለመግዛት የሚያስችል ሥርዓት ነው። ይህን በእንስሳቱ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በቀላሉ መከላከል ያስችላል፡፡

በዓመት ሁለት ጊዜ ዋስትና እንዲሸጥ ይደረጋል ያሉት አቶ ጀማል፤ በዚህም አርሶ አደሩ በድርቅ ወቅት የሚደርስበትን ኪሳራ የእንስሳት መድኅን ዋስትና በመግዛት ሊያካክስ ይገባል ብለዋል።

የመጀመሪያው ዙር የእንስሳት መድን ዋስትና ሽያጭ ነሐሴ 26 ቀን 2016 ዓ.ም የጀመረ ሲሆን መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የገለጹት አቶ ጀማል፤ የዚህ ዋስትና ተጠቃሚ ለመሆን በተቀመጠው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የዋስትና ክፍያውን ማለትም የአጠቃላዩን 30 በመቶ ክፍያ ማስገባት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ይህ ክፍያ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ሲሆን ቀሪውን 70 በመቶ ደግሞ መንግሥት ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር እንደሚሸፍን የተናገሩት አቶ ጀማል፤ ይህም አርብቶ አደሩ በድርቅ ምክንያት እንስሳቱን እንዳያጣ እና የሚያጋጥመውን ኪሳራ እንደሚከላከል ገልጸዋል።

በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከናወነው የእንስሳት መድኅን ዋስትና ሽያጭ በዚህ ዓመት ለ80 ሺህ አርብቶ አደሮችን ተደራሽ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ዙር ለ35 ሺህ አርብቶ አደሮች ዋስትና ለመስጠት ታቅዷል ነው ያሉት።

የአርብቶ አደሩ 30 በመቶ ክፍያ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ መሆኑን የተናገሩት አቶ ጀማል፤ ዋስትናው የሚተገበረው በዓለም ባንክ ድጋፍ እና በግብርና ሚኒስቴር አማካኝነት በተቋቋመው የአርብቶ አደሮች የአደጋ ቅነሳና አካታች የኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት አማካኝነትና በአጋር ድርጅቶች እገዛ መሆኑን ጠቁመዋል።



# “የአፍሪካ አዳራሽ” ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ በመታደስ ላይ ይገኛል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- “የአፍሪካ አዳራሽ” ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ዘመኑን የዋጀ ገጽታ እንዲላበስ ተደርጎ በመታደስ ላይ እንደሚገኝ በተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አስታወቀ። በመጭው ጥቅምት ወር አጋማሽ እንደሚመረቅም ተጠቁሟል፡፡

በተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የአፍሪካ አዳራሽ አስተዳደር የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አንቶንዮ ባእዮ የእድሳቱን ሂደት ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ባስጎበኙበት ወቅት እንደገለጹት፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መሥራቾች የመጀመሪያ ጉባኤያቸውን ያካሄዱበት ታሪካዊው “የአፍሪካ አዳራሽ” እድሳቱን በማጠናቀቅ በመጭው ጥቅምት 11 ቀን 2017 ዓ.ም ይመረቃል፡፡

እድሳቱ ከ61 ዓመታት በላይ የቆየውን አዳራሽ ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ዘመኑን የዋጀ ገጽታ እንዲላበስ እያስቻለው እንደሚገኝም የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ በተለይም የአፍሪካን ታሪካዊ አመጣጥ፣ አሕጉሪቱ አሁን ያለችበትን እና የወደፊት ሁኔታ የሚያሳይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አዲሱ የእድሳት ዲዛይን ዘላቂ፣ ማራኪ እና ጎብኚዎችን በሚስብ መልኩ የተቀረጸ መሆኑን አንስተው፤ ብዛት ያለው የሕንፃው ክፍል በአዲስ እንደተተካና የተሠራው ሥራ ሕንጻውን የማደስ ብቻ ሳይሆን የማዘመን ተግባርንም እንደሚያጠቃልል ጠቁመዋል፡፡

ለእድሳት ሥራው 57 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ በጀት እንደወጣና ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ ብቃት ያላቸው ኮንትራክተሮች እድሳቱን በልዩ ትኩረት እያከናወኑት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ እድሳቱ የአፍሪካ ታሪክ እና ትዝታ ጋር የተያያዘ መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለፃ፤ ከሕንፃው ዲዛይን በስተጀርባ ካሉት ዋና ዋና መርሆዎች ውስጥ አንዱ የአፍሪካን ታሪክ ባከበረ መልኩ እድሳቱን ማከናወን ነው፡፡ የእድሳት ሥራው ዓላማ ሕንጻው ወደነበረበት መመለስ ላይ ያተኩራል፡፡

እድሳቱ በሥነ ሕንፃ፣ በባሕልና ታሪካዊ እሴትን በጠበቀ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን በመግለጽ፤ በጄኔቫና በኒውዮርክ ከሚገኙ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጋር ተወዳዳሪነት እንዲኖረው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

የአፍሪካ አዳራሽ ፕሮጀክት የሲቪል እና አርክቴክቸራል ሥራዎች ሱፐርቫይዘር ኢንጂነር ጌታቸው አርዓያ በበኩላቸው፤ ሕንጻው በራሱ ቅርስ መሆኑን በመግለጽ እድሳቱ የአዳራሹን የሥነ-ሕንፃ ውበት ወደነበረበት እንዲመለስ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ አንድነት እና የእድገት ምልክት የሆነውን ቦታ ዘመናዊ እንዲሆን በማስቻል ለጉብኝት ክፍት ለማድረግ ነው ብለዋል፡፡

አዳራሹ ፓን አፍሪካኒዝም ተቋማዊ ቅርጽ የያዘበት ቦታ መሆኑን የገለጹት ሱፐርቫይዘሩ፤ አፍሪካውያን በጉዳዮቻቸው ዙሪያ የመከሩበት የመጀመሪያው ስፍራ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ኢንጂነር ጌታቸው ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ የሕንጻውን መዋቅራዊ ደኅንነት በማረጋገጥ ለቀጣይ ተጨማሪ ዓመታት እንዲቀጥል ማድረግ፣ የኮንፈረንስ ሥርዓቱን ማዘመን፣ የሕንጻውን ቅርስነት ማስጠበቅና ሕንጻው ለማኅበረሰቡ ክፍት እንዲሆን ማስቻል ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአደባባይ በዓላት የሠላምና የአብሮነት መገለጫ፣ የቱሪዝምም አቅም ሊሆኑ ይገባል!

ኢትዮጵያ በርካታ ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ እሴትን የተላበሱ በዓላት ባለቤት ናት፡፡ እነዚህ በዓላት ደግሞ አንድም ሀገራዊ ገጽታን ተላብሰው የሚከበሩ፤ በሌላም መልኩ አካባቢያዊ እና ማኅበረሰባዊ ገጽታን ይዘው የሚከወኑ ናቸው፡፡ ከአካባቢያዊ እና ሀገራዊ ገጽታቸው አለፍ ሲልም፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባሕል፣ የቋንቋ እና የታሪክ ተቋም (ዩኔስኮ) በዓለም ቅርስነት መዝገቦ የያዛቸውም በርካታ ናቸው።

በተለይ ከእነዚህ ሃይማኖታዊም ሆኑ ባሕላዊ በዓላት በአመዛኙ የአደባባይ በዓል እንደመሆናቸው፤ እነዚህ በዓላት ከፍ ያለ ማኅበራዊ መስተጋብር፣ የእርስ በእርስ መተሳሰብና አብሮነት የሚገለጽባቸው ናቸው፡፡ ይሄ አብሮ መዋልና በዓላትን በጋራ የማክበር ሂደት ደግሞ በአንድም ከፍ ያለ ሠላምን የሚሻ፤ ሁለተኛም የሕዝቦች ዘርፈ ብዙ የባሕል ትሩፋቶች የሚንፀባረቅበት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ እነዚህ የአደባባይ በዓላት በአንድ በኩል የሕዝቦች አብሮነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በሕዝቦች አብሮነት ውስጥ ደምቆ የሚታይ የባሕል (የቋንቋ፣ የአለባበስ፣ የባሕላዊ ክዋኔዎችና ሌሎችም) ክዋኔዎች ዓውድም ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ይሄ የአብሮነት እና የባሕል ክዋኔ ዓውድነቱ ተጣምረውና ከፍ ብለው እንዲገለጡ የሚያደርጋቸው የሠላም ድባብን የሚፈልጉም ናቸው፡፡

እነዚህ በዓላት ጎልተው ከሚገለጡባቸው ወራት መካከል ደግሞ መስከረም አንዱ ነው፡፡ ወርሐ መስከረም የዘመን መለወጫ በዓልን ጨምሮ፣ የመስቀል፣ የኢሬቻ፣ ዮዮ መስቀላ፣ ያሆዴ፣ ጊፋታ እና ሌሎችም ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ በዓላት የሚከበሩበት ነው፡፡ እነዚህ በዓላት ደግሞ በዋናነት ሕዝቦች በአብሮነት ወጥተው የሚያከብሯቸው የአደባባይ በዓላት ናቸው፡፡

ከዚህ አኳያ እነዚህ የአደባባይ በዓላት በአንድ በኩል ኢትዮጵያ የብዝኃነት ዓውድ መሆኗ የሚገለጽባቸው ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል ይሄ ብዝኃነት ከፍ ያለ ድምቀትን የተላበሰ ኢትዮጵያዊ ቀለም መገለጫዎች ናቸው። ለዚህም ነው በእነዚህ በዓላት የበዓሉ ባለቤት ከሚባለው የሃይማኖት ተከታይ ወይም የባሕሉ ባለቤት ከሚባለው ብሔርና ሕዝብ ባሻገር ያሉ ሃይማኖቶችና ብሔሮች ተሳታፊ ሆነው የሚገለጡበት፡፡

እነዚህ በዓላት የአደባባይ በዓላት እንደመሆናቸው፤ የበዓላቱ ተሳታፊዎች ደምቀው ሊታዩባቸው የሚያስችሏቸውን አልባሳትና ጌጣጌጦች ባሕልና እምነታቸው በፈቀደላቸው ልክ ተውበው የሚታዩት። ማንነትና እሴታቸውን ሊያሳይ በሚያስችላቸው ኅብረትም ባሕላዊ ጭፈራዎችና ክዋኔዎች ታጅበው የሚያከብሩት፡፡

ይሄ ሁነት ደግሞ ለበዓላቱ ከፍ ያለ ድምቀትና መስሕብን የሚያጎናጽፍ ነው፡፡ አልባሳቱ፣ ጌጣጌጥና ጭፈራዎቹ ተዳምረው የሚፈጥሩት ኅብር ለተመልካቹ ቀልብን የሚይዝ፤ ልብን በሐሴት የሚያረሰርስ ነው። ለዚህም ነው እነዚህ በዓላት በደረሱ ቁጥር ከውስጥም፣ ከውጪም የጎብኚዎች (ቱሪስቶች) ቁጥር ሲጨምር የሚታየው፡፡

ምክንያቱም፣ ጎብኚ ለዓይኑ የሚስብ ነበር ይፈልጋል፤ ልቡን የሚያስደስትነት፣ ለነፍሱም ሐሴትን የሚያጎናጽፈው ሁነት ይሻል፡፡ በኢትዮጵያ ያሉ የአደባባይ በዓላት ደግሞ እነዚህን በሙላት የሚሰጡ ዓውዶች ናቸው፡፡ በአልባሳቱ የተማረከ ዓይንን፤ በጭፈራዎቹ ክዋኔ የተደመመ ልብን፤ በሃይማኖታዊ ሁነቶቹ የተመሰጠች ነፍስን፤ በእነዚህ በዓላት መመልከት የተለመደ የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡

ይሄ ብቻ አይደለም፣ እነዚህ በዓላት በሕዝቦች ከፍ ያለ የአብሮነት እና ወንድማማችነት ስሜት ታጅበው የሚከበሩ እንደመሆናቸው፤ ከድምቀትና ውበትነታቸው ባሻገር የሠላም ዓውድነታቸውም ጎልቶ የሚጠቀስ ነው፡፡ ይሄ ሠላማዊ ሁነትም ነው በየጊዜው ቱሪስቶች በብዛት በበዓላቱ ላይ እንዲገኙና እንዲሳተፉ እያደረገ የሚገኘው፡፡

አሁን ያለንበት መስከረም ወር ደግሞ፣ እነዚህ በዓላት የሚከበሩበት እና የበዓላቱ ሁነቶች በብዛት የሚታዩበት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ እነዚህን ሃይማኖታዊም ሆኑ ባሕላዊ የአደባባይ በዓላት፤ በአንድ በኩል የአብሮነት መድረክነታቸው፤ በሌላ በኩል ኅብረ ብሔራዊነታቸው የሚፈጥረው የውበት ስገነት መገለጫነታቸው፤ አለፍ ሲልም የቱሪዝም መስሕብነታቸው ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ይሄ እንዲሆን ደግሞ የበዓላቱን የሠላም እሴት ዓውድነት ከፍ ባለ መልኩ እንዲገለጥ ማስቻል ይገባል። ምንም እንኳን ሕዝቡ የሠላሙ ባለቤት ሆኖ በዓላቱን የሚከውን ቢሆንም፤ እነዚህን ዓውዶች ለሌላ የፖለቲካ ትርፍ ለማዋል የሚፈልጉ ኃይሎች ይጠፋሉ ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በዓላቱ ከቀደሙት ጊዜያት ከፍ ባለ እሴታቸውን ጠብቀው እንዲከወኑ፤ የአብሮነት እና ወንድማማችነት መገለጫነታቸውን እንዲመሰክሩ፤ የቱሪዝም መስሕብነታቸውም ከፍ እንዲል ለማስቻል፤ ከዚህ በተቃራኒው ሊፈጸሙ የሚችሉ ጉዳዮችን ከወዲሁ መገንዘብና ሠላማዊነቱን ጠብቆ እንዲከናወኑ ማድረግ ከሁሉም አካል የሚጠበቅ ትልቅ የቤት ሥራ ይሆናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኢነርጂ ዲፕሎማሲ ትልቁ የቤት ሥራችን

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

> **ኢትዮጵያ ከኃይድሮ ኤሌክትሪክ ባለፈም በሶላር ኢነርጂው በሰፊው አቅም ያላት ሲሆን ወደ ምርት በአግባቡ አልተገባም። በዘርፉ ላይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመርቂ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን በበቂ ሁኔታ አከናውነዋል ማለት አያስደፍርም**

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ኢትዮጵያ ካላት የታዳሽ ሃብት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው 10 በመቶ ብቻ ነው። ይህ ማለት ገና ነገሮች ሁሉ በጅማሮ ላይ ናቸው፡፡ ብዙ ሊገኝበት፤ ብዙ ሊታፈስበት በሚገባው ዘርፍ ላይ ወደ ኋላ ቀርታለች፡፡ ይህ የሆነው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም ችግሩን ውስጣዊ እና ውጫዊ መሆናቸውን በማሳያዎች ማስረዳት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ በታዳሽ ኢነርጂ ላይ በሰፊው ወደ ልማት ለመግባት በምታደርገው ጥረት በርካታ ውጫዊ ፈታኝ ሁኔታዎች ተደቅነውባታል፡፡ በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ይህን እውን እንዲሆን መፍቀድ ቀርቶ ዓላማውን በሐሳብ ደረጃ መኖሩ በራሱ የማያባራ የራስ ምታታቸውን ይቀሰቅስባቸዋል፡፡ ይህን መሰል ሀሳብ ሲሰሙም መፈጠራቸውን ይጠላሉ፤ ከውስጣቸው ያንዘረዝራቸዋል፡፡

ለአብነትም ኢትዮጵያ ካላት ከፍተኛ የታዳሽ ኃይል ውስጥ አንዱ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ (ከውሃ የምታመነጨው) ኃይል እጅግ ግዙፍ አቅም ያላት መሆኑ ነው፡፡ ይህን እውን እንዳይሆን በርካታ የኢትዮጵያ ጠላቶች በእያንዳንዱ ሥራ እግር በእግር እየተከታተሉ የማደናቀፍ ሙከራዎችን እያደረጉ ነው። ለዚህ ማሳያ ጥቂት ምሳሌዎችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ሁኔታው ያልተዋጠላቸው አካላት ኢትዮጵያን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የማወክ ሥራ ላይ ተጠምደዋል፡፡ ውሣኝ በሚባሉ ዓለም አቀፍ የፖለቲካ መድረኮች ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ጀምሮ በስውር ዲፕሎማሲ ጫና ብሎም ጂኦ-ፖለቲክስ በማወክ እጃቸውን ያስረዘሙ ሀገራት በርካቶች ናቸው፡፡ አሁናዊ የምሥራቅ አፍሪካ የፖለቲካ ትኩሳት በተለይም የግብፅ በሞቃዲሾ አምባ ዙሪያ መሽከርከር ዋነኛ ምክንያት ይኸው ነው ፡፡

በአሁኑ ወቅትም ምሥራቅ አፍሪካን ማወክ እና በአብዛኛው ደግሞ ኢትዮጵያን ከጉዞዋ መግታት የሚለው እሳቤ የዚሁ አኩይ ተግባር አካል ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ በግልገል በለስ ላይ ሲካሄድ የነበረውም ልማት ለማደናቀፍ ሲደረግ የነበረው ሙከራም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ በተመሳሳይ ጊቤ እና ሌሎች የኃይድሮ ኤሌክትሪክ የኃይል ማመንጫ ግንባታዎች ሂደት ላይ ኢትዮጵያን በከፋ ሁኔታ እንድትፈተን አድርገዋታል፡፡

ዓለም አቀፍ የገንዘብ አበዳሪ ተቋማትን በር በማንኳኳት ብድር ከማስከልከል እስከ ዲፕሎማሲያዊ ጫና ያልሞከሩት አማራጭ፤ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም፡፡ ይህ የታሪካዊ ጠላቶች አካሄድ በቀጣይም ይበልጥ በእልህ የሚገፉበት እንጂ አሜን ብለው የሚቀበሉት አለመሆኑን ብዙ አስረጂዎችን በመጥቀስና ቢሆኖችን በማስቀመጥ ሁኔታዎችን ከዚህ በላይ መተንተን ይቻላል፡፡

ውጫዊ ጫናዎች እንደተጠበቁ ሆነው ውስጣዊ ችግሮችን መመልከትም አስፈላጊ ነው፡፡ ኢነርጂውን ወደ ቢዝነስ በመቀየር ብሎም ማኔጅ ማድረግና ሥርዓት መገንባት ላይ እንደ ሀገር ብዙ አልተሠራበትም፡፡ ኢትዮጵያ በታዳሽ ኃይል ኢነርጂ ትልቅ ዲፕሎማሲ መሥራት ትችላለች፡፡ የቀጣናው ሀገራትን ጨምሮ በርካታ አፍሪካ ሀገራት በታዳሽ ኃይል አቅም ከኢትዮጵያ አይስተካከሉም፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎች ሀገራትም የኤሌክትሪክ ኃይል አሻግሮ ለመሸጥ ስትራቴጂክ ቦታ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመጥር የሆኑ ምሑራንና እና ጥናቶችም የሚያመለክቱት ኢትዮጵያ የታዳሽ ኃይል ቋት መሆኗ ነው፡፡ ዳሩ ግን ይህን ሀብት አውጥቶ ለመጠቀም በመጀመሪያ ደረጃ ዕውቀትና ቴክኖሎጂ በሀገሪቱ በስፋት ሥራ ላይ እየዋለ አይደለም፡፡

በሌላኛው በኩል ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ቀጣይነት ያለው የተረጋጋ ሠላም አለመስፈን ባለሀብቶች በዘርፉ በስፋት እንዳይሳተፉ እንቅፋት ሆኗል፡፡ በተጨማሪም የፖለቲካው ፍኖተ ካርታ እና የማኅበረሰቡ እሳቤ ብሎም የምጣኔ ሃብት ዕድገት እየተጓዘበት ያለው ሐዲድ የተራራቀ መሆን ሁኔታዎችን የበለጠ አስቸጋሪ አድርገውታል፡፡

ኢትዮጵያ ከኃይድሮ ኤሌክትሪክ ባለፈም በሶላር ኢነርጂው በሰፊው አቅም ያላት ሲሆን ወደ ምርት በአግባቡ አልተገባም፡፡ በዘርፉ ላይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመርቂ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን በበቂ ሁኔታ አከናውነዋል ማለት አያስደፍርም፡፡ በባሕሪው የኢነርጂ ዘርፍ ቅንጅታዊ አሠራር ይፈልጋል፡፡ በዚህ ላይም በበቂ ሁኔታ አመሠራቱን ከሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ በታዳሽ ኃይል ላይ ለመሥራት፤ ካላት ሃብት በላይ ያላት የአየር ንብረት በጣም ምቹ የሚባል እና ሌሎች አልሚዎችን ለመሳብ የሚያስችል ነው፡፡ በዘርፉ ላይ በትክክል የተቀመጡ እና የተቀናጁ ብሎም ምሑራዊ እሳቤዎችንና ትንታኔዎችን ያካተቱ ዶክመንቶች በቀላሉ አይገኙም፤ ቢገኙም በጣም በተቆራረጠ እና ቅንጅት በጎደለው መልኩ ነው፡፡

በተለይም ደግሞ የግል ባለሀብቶች በዚህ ዘርፍ እንዲሰማሩ ሰፋ ያለ መግቢያ እና ዕድል ሊመቻች ይገባል፡፡ ይህ አንድም ባለሀብቶች ሀገራዊ አቅሙን ተጠቅመው በብዛት ኢነርጂ እንዲያመርቱ ያስችላል፤ ኃይሉ ታዳሽ በመሆኑ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ቢውልም ታዳሽ ካልሆኑ የኢነርጂ ምንጮች አኳያ አዋጭ መሆኑም ዘላቂ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡ ዘርፉ ልዩ ትኩረት ከተሰጠው ሚሊዮን ዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥርም ይታመናል፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ ታዳሽ ያልሆኑ ኃይሎች ጥቅም ላይ ውለው ወይንም የአገልግሎት ዘመናቸው ሲያበቃ ብሎም ተረፈ ምርቶችን ለማስወገድ ከፍተኛ ወጪ መጠየቁ፤ ታዳሽ ያልሆኑ ኃይሎች መጠቀም ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ወይንም ገንዘብ የሚጠይቅ መሆኑ በቋሚነት ሀብት እንዲመደብለት ያስገድዳል፡፡

ለአብነት ኢትዮጵያ የነዳጅ ምርቶች ለማስገባት በዓመት በአማካይ 6ነጥብ4 ቢሊዮን ዶላር ወጪ ታደርጋለች፡፡ ይህ እጅግ ከፍተኛ የሚባለው ነው፡፡ ይህንን ሀገራዊ ወጪ ለመቀነስ ሆነ ለማስቀረት በታዳሽ ኃይል ላይ በሰፊ መሥራት እና በቀጣናው የኢነርጂ ተደራሽነት ላይ ማተኮር አዋጭ ነው፡፡ በተለይም አጀንዳ 2063 ለማሳካት በዋናነት ከጠቀመጡ ግቦች አንዱ አፍሪካ በኢነርጂ መሠረተ ልማት ማስተሳሰር መሆኑም እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ የሚታይ ነው፡፡

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር፤ ኢትዮጵያ በዘርፉ ካላት እምቅ አቅም አኳያ ብዙ መሥራት የሚጠበቅባት ቢሆንም ጎን ለጎን የዘርፉ ተጠቃሚ እንዳትሆን ጠላት የሚሸርባቸውን ማለቂያ የሌላቸው ሴራዎች አውቆ ተዘጋጅቶ የመመከት ሥራዎችን በስፋት መሥራት ይጠበቅባታል ።

ለዚህ ደግሞ ለኢነርጂ ዲፕሎማሲ ትኩረት በመስጠት የቀጣናውን ሀገራት ስስ ብልት ማወቅና በሰጥቶ መቀበል መርሕ ወዳጅን በሁሉም መስክ ማፍራት እጅግ አስፈላጊው ነው፡፡ ዲፕሎማሲው በየዘርፉ አስረጂ ሁኔታዎችን ይፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ የኢነርጂ ዲፕሎማሲ የኢትዮጵያ ትልቅ የቤት ሥራ መሆን አለበት ፡፡

# "በቀጣናው ያሉትን የቱሪዝም ሀብቶች በትብብር በማልማት ለተተኪው ትውልድ ማሻገር ይገባል"

- ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር) የኢጋድ ዋና ጸሐፊ

**ሄለን ወንድምነው**



ፎቶ: ሃዲስ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- በቀጣናው ያሉትን የቱሪዝም ሀብቶች በትብብር በማልማት ለተተኪ ትውልድ ማሻገር ይገባል ሲሉ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ኢጋድና አባል ሀገራቱ ዘላቂ የቱሪዝም ልማትን ዕውን ለማድረግ ያዘጋጁት የ10 ዓመት ዘላቂ የቱሪዝም መሪ ዕቅድ (ማስተር ፕላን) በትናንትናው ዕለት ይፋ ተደርጓል፡፡

የኢጋድ ዋና ጸሐፊ ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ የኢጋድ አባል ሀገራት የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ ባሕል፣ ዕሴትና ወግ የተትረፈረፈበት ቀጣና ነው።

በቀጣናው ያሉትን የቱሪስት ሀብቶች በሚፈለገው ደረጃ በማልማት ለመጠቀም እና ለትውልድ ለማሻገር በትብብር መሥራት እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

በኢጋድ አባል ሀገራት በሚፈጠሩ የፀጥታ ችግሮች ምክንያት የቀጣናውን ባሕል፣ ወግ፣ እሴት እና የተፈጥሮ ሀብቶችን በሚፈለገው ደረጃ መጠቀምና ማስተዋወቅ አልተቻለም ያሉት ጸሐፊው፤ በቀጣይ የቀጣናውን ሀገራት ሠላም በማስፈንና መሠረተ ልማትን በማስፋፋት ከቱሪዝም ዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል።

የኢጋድ አባል ሀገራት የተለያየ አይነት የቱሪዝም ሀብት ያላቸው ሲሆን፤ የቱሪዝም ሀብቶቹን በጋራ ለማልማትና ለመጠቀም፣ የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማጠናከር፣ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ (ማስተር ፕላን) መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

የተዘጋጀው ማስተር ፕላን እ.ኤ.አ ከ2024 እስከ 2030 የሚተገበር ሲሆን፤ ለቱሪዝም መሠረተ ልማት መስፋፋት፣ ለመረጃ ልውውጥ፣ የዘርፉን ተግዳሮት ለመፍታት እንዲሁም በአባል ሀገራቱ መካከል ነፃ የቪዛ ሥርዓት እና ወጥ የሆነ የቱሪዝም ፖሊሲና አሠራር እንዲኖር ያስችላል ብለዋል።

ማስተር ፕላኑ የቀጣናውን ሀገራት በቱሪዝም ዘርፉ ተወዳዳሪ ለማድረግ ጉልህ ሚና ያለው በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በኃላፊነት እንዲሠሩ አሳስበዋል፡፡

ቱሪዝም በሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር፣ ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የቀጣናው ሀገራት የቱሪዝም ዘርፉ የሚያበረክተውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በአግባቡ በመረዳት ማስተር ፕላኑን ተፈጻሚ ማድረግ፣ ሠላምን ማስፈንና የተጠናከረ የመንገድ፣ የአየርና የባሕር መሠረተ ልማትን ማስፋፋት እንደሚጠበቅባቸው አስታውቀዋል።

ኢጋድም በቀጣናው ሀገራት መካከል የተጠናከረና የተሳለጠ መሠረተ ልማት እንዲኖር የተለያዩ አጋር አካላት በመሠረተ ልማት ግንባታው ኢንቨስት እንዲያደርጉ የማግባባት ሥራ እንደሚሠራ አመላክተዋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ናሲሴ ጫሊ በበኩላቸው፤ በቀጣናው ያሉት የቱሪስት ሀብቶች በአግባቡ ካለመልማታቸውና ካለመተዋወቃቸው ባለፈም በተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች፣ ነፃ ቪዛና የሠለጠነ የሰው ኃይል ባለመኖሩ በዘርፉ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ መሆን አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

አሁን ላይ የቀጣናው ሀገራት ዘርፉን በማልማትና በማስተዋወቅ ተጠቃሚ ለመሆን የ10 ዓመት ዘላቂ የቱሪዝም ማስተር ፕላን ያዘጋጁ ሲሆን፤ ለማስተር ፕላኑ ተግባራዊነት ኢትዮጵያ ከሌሎች የአባል ሀገራት ጋር በቅንጅትና በቁርጠኝነት እንደምትሠራ አስታውቀዋል።

የቀጣናው ሀገራት ከቱሪዝም ዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን የቱሪዝም መሠረተ ልማትን በማስፋፋት፣ መዳረሻዎችን በማልማትና በማስተዋወቅ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ጎብኚዎችን ለመሳብ በትብብር መሥራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፉን ከአምስቱ የልማት ምሰሶዎች ውስጥ በማካተት እየሠራች መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችንና የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት የማልማት፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ እና ሌሎች በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተሠሩት ሥራዎችም ኢትዮጵያ የቱሪስት መዳረሻነቷ እያደገ የመጣ ሲሆን፤ የቀጣናው ሀገራት ያላቸውን ተሞክሮ ማጋራትና ድንበር ተሻጋሪ የቱሪዝም ልማት ላይ በትብብር መሥራት እንደሚጠይቅ አስረድተዋል፡፡

# "የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለመሳተፍ የሚያስችላትን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቋንም ገልጸዋል።

ጉባዔው የተመድ ዘላቂ የልማት ግቦች ተግዳሮት ውስጥ በገቡበት ጊዜ መካሔዱ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ አድርጎታል ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ በጉባኤው ብሔራዊ ጥቅሞቿን እና አፍሪካን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ታደርጋለች። በጉባኤው ይፀድቃሉ ተብሎ የሚጠበቁ ሰነዶች በቀረቡባቸው ሁነቶች ላይም ስትሳተፍ ቆይታለች ብለዋል።

ከጉባኤው ጎን ለጎን የብሪክስ አባል ሀገራት ስብሰባ እና ከተለያዩ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚደረጉ ውይይቶች እንደሚኖሩና በኢትዮጵያ በኩል ሰፊ ዝግጅት መደረጉንም አንስተዋል። ከአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ተልዕኮ በሶማሊያ ሠራዊት አዋጭ ሀገራት ጋር የጎንዮሽ ውይይት እንደምታደርግም አመላክተዋል፡፡

አምባሳደር ነብያት ከኢኮኖሚና ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ጋር በተያያዘ የመግለጫቸው ክፍል፤ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ይበልጥ በማሳለጥ በ2017 ዓ.ም. በቱሪዝም ዲፕሎማሲ የኮንፍረንስ ቱሪዝም እንዲስፋፋ አቅጣጫ አስቀምጠን እየተንቀሳቀስን ነው ብለዋል።

አክለውም፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ሩቅ ምሥራቅ አካባቢ በበየነ መረብ በሚንቀሳቀሱ ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች አዲስ እንቅስቃሴ እየታየ ነው። በዚህም ዜጎች እየተጭበረበሩ ወደ ሞት ቀጣና እያመሩ ይገኛሉ። ሕገወጥ አካላቱ ከድርጊታቸው ሊታቀቡ ይገባል፤ ኅብረተሰቡም በተጭበረበሩ መረጃዎች መታለል የለበትም ብለዋል።

# የሠላማዊ ትግል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አገልግለዋል፡፡ በማስተማርና ምርምር ላበረከቱት ሙያዊ አስተዋፅዖ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ አግኝተዋል።

የደርግ መንግሥት ወርዶ የኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ሲቋቋም በየነ (ፕ/ር)፣ ምክትል የትምህርት ሚኒስትር ሆነው ለአጭር ጊዜ አገልግለዋል።

ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ የትውልድ አካባቢያቸው እንደራሴ በመሆን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነዋል። ከ30 ዓመታት በላይ በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ በከፍተኛ አመራርነት ተሳትፈዋል።

ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ጀምሮ ባሉት የሀገሪቷ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፋቸው የሚገለጸው ፕሮፌሰር በየነ፤ በኋላም በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ሲሠሩ ቆይተዋል።

ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ሕይወታቸው እስካለፈበት ዕለት ድረስ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን በዋና ዳይሬክተርነት ሲያገለግሉ ነበር፡፡ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው መስከረም 7 ቀን 2017 ዓ.ም ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን፣ መስከረም 9 ቀን 2017 ዓ.ም በጴጥሮስ ወጳውሎስ መካነ መቃብር ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሚሊኒየምም አዳራሽ በተካሄደው የበየነ ጴጥሮስ (ፕ/ር) የአስከሬን ሽኝት መርሐ ግብር ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ሀገርን መውደድ፣ ተግቶ መሥራትን ቀጣዩ ትውልድ ከበየነ (ፕ/ር) ታሪክ ሊማር ይገባል ብለዋል፡፡

በየነ (ፕ/ር) በሕይወት በነበሩበት ወቅት ታታሪና ሀገር ወዳድ ምሑር እንደነበሩ አስታውሰው፤ ለሀገራቸው በርካታ ሥራዎችን ሠርተው አልፈዋል፤ ይህ ሥራቸውም ከመቃብራቸው በላይ ሲታወስ ይኖራልም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ሁላችንም እንደእርሳቸው ጊዜ ሳናባክን ለሀገር ጠቃሚ ሥራዎችን ሠርተን ማለፍ አለብን ሲሉ ዐቢይ (ዶ/ር) መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የሥራ አስፈጻሚ አባልና የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ምክትል ሊቀ መንበር ራሔል ባፌ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤ በየነ (ፕ/ር) የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፈታኝ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለሕዝብ ድምፅ ሆነው መቆም የቻሉ ሰው እንደነበሩ አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያን አብዝተው የሚወዱና ስለኢትዮጵያ በተጠሩበት ጊዜ ሁሉ ቀድመው መገኘት መገለጫቸው እንደነበር የገለጹት ራሔል (ዶ/ር)፤ ምክትል ሚኒስትር ሆነው የሚኒስትርነት ደመወዝ፣ የሕዝብ ተመራጭ ሆነውም የተመራጭነት ጥቅማጥቅም አልፈልግም ብለው በመምህርነት ደመወዛቸው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ማገልገላቸውንም አንስተዋል።

ሁላችንም ቅንነት፣ መልካምነትና ሀገርን መውደድ ምን እንደሆነ ከበየነ ጴጥሮስ (ፕ/ር) ልንማር ይገባል ብለዋል፡፡

# በምርኩዝ መራመድ መቄዶንያን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጀግኖች አርበኞች ማኅበር አባላት በምርኩዝ መሄድ መቄዶንያን ከመርዳት አይገታንም በማለት በማዕከሉ ተገኝተዋል፡፡

እነዚህ የሀገር ባለውለታዎች የዕድሜ ባለፀግነታቸው እና ባሳለፉት ውጣ ውረድ ምክንያት ለራሳቸው እርዳታ የሚፈልጉ ቢሆንም መቄዶንያ ከሚገኙ ወገኖች ጋር ያላቸውን ተካፍለው ለማሳለፍ በቂ ሞራል አላቸው፡፡

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር በመቄዶንያ በመገኘት ለማኅበሩ አባላት የምሳ ግብዣ ያደረጉ ሲሆን፤ ግብዣውን ያደረጉት ለአዲስ ዓመት መዋያ ተብሎ ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ለአርበኞች ማኅበር ከተሰጠ የበዓል ስጦታ መሆኑን የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ይናገራሉ፡፡

‹‹እኛ አቅማችን ቢደክምም በምርኩዝ ብንራመድም ሞራላችን ግን መቄዶንያ የሚገኙት አቅመ ደካሞች ወገኖቻችን ለመርዳት በቂ ነው›› ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በውስጣችን ፍቅርና ሠላም ካለ ተካፍለን እንበላለን ብንታመምም የሚያሳክመን አናጣም ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን ለእምነታቸው እና ለባሕላቸው ቦታ የሚሰጡ በመሆናቸው ይህን የመሰለ የአረጋውያን መርጃ ማዕከል እና ኃላፊነት ተሰምቶት በርህራኄ የሚያገለግል የክብር ዶክተር ቢኒያምን ማግኘት ትልቅ ስጦታ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም እርስ በርስ በተገኘው አቅም በመረዳዳት ለማኅበሩ አባላት አስተዋፅዖ ማድረግ የሞራል ግዴታ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር በዓመት ሦስት በዓላትን እንደሚያከብር የሚናገሩት ፕሬዚዳንቱ፤ ሚያዚያ 27 የድል በዓል፣ የካቲት 12 ግራዚያኒ በአዲስ አበባ ከተማ የጨፈጨፋቸው ንፁሓንን ለመዘከር እና ዋነኛው የኢትዮጵያ ታሪክ በወርቅ ቀለም ያስፃፈው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ቀን ተጠቃሽ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም መቄዶንያ ከሚገኙት አቅመ ደካሞች መካከል በጦር ሜዳ ቆይታቸው ከውስጣቸው ጥይት ተለቅሞ ያላለቀ ጀግኖች መኖራቸውን መርሳት እንደሌለበት ያስረዳሉ፡፡

የማኅበሩ አባል እና የምክር ቤት አባል የሆኑት ወይዘሮ ትግስት ኃይሌ በበኩላቸው፤ ትውልድ እና ዕድገታቸው አዲስ አበባ ኮሪያ ሰፈር መሆኑን ጠቅሰው፤ ወላጅ አባታቸው የጀመሯቸውን የጀግንነት ሥራዎች ሳይፈፅሙ በማለፋቸው እሳቸውም የአባታቸው ፈለግ በመከተል እያገለገሉ እንደሚገኙ ይናገራሉ፡፡

የማኅበሩ አባላት በድኅማ የሚተዳደሩ ቢሆንም ለአዲስ ዓመት ከተሰጠን ላይ ተካፍለን ለማሳለፍ መቄዶንያ መገኘታቸውን ይገልፃሉ፡፡ መቄዶንያ የሚገኙት ወገኖች ከምንም በላይ የሰው ፍቅር የሚያስፈልጋቸው ስለሆኑ ባለን አቅም ሁላችንም እዚህ በመገኘት በገንዘብና በጉልበት መርዳት ቢቻል መልካም መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በተመሳሳይ የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ በቀለ ሻረው፤ ማህበሩ ከ86 ዓመት በፊት የጣሊያን ወራሪ ሀገራችንን በወረረበት ወቅት በመንዝ እና ተጉለት አንቀላፊ በተባለ ቦታ መመሥረቱን ጠቅሰው፤ በወቅቱ በተናጠል የነበረውን ውጊያና ትግል በአንድነት በመሆን ጠላትን ለማዳከም እንደተመሠረተና እስከ መጨረሻው ድረስ ሀገርን ነፃ ያወጣ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡



መቄዶንያ በአሁኑ ሰዓት ትልቅ ዓላማ ያለው እና በተግባር ሥራውን እያስመሰከረ የሚገኝ ማኅበር በመሆኑ የአርበኞች ማኅበርም ከበፊት ጀምሮ ተካፍሎ መብላትን የሚያውቅ በመሆኑ ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተሰጠ የበዓል ስጦታ በማካፈል ከወገኖቻችን ጋር አብሮ ማሳለፍ መቻሉን ያብራራሉ፡፡

መቄዶንያን ቀደም ሲልም እየመጡ እንደሚጎበኙ ጠቅሰው፤ ማኅበሩ ሰፊ ወጪ እያወጣ ደካሞችን እያገዘ እና በሌሎች ክልሎችም ቅርንጫፎች እያስፋፋ በመሆኑ ከፍተኛ ድጋፍ እና እገዛ ስለሚያስፈልገው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ማገዝ አለበት ይላሉ፡፡

የመቄዶንያ መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ የክብር ዶክተር የሆኑት ቢኒያም በለጠ በበኩላቸው፤ መቄዶንያ ውስጥ የሚገኙ አረጋውያን ተከብረው እንደሚኖሩ እና የጤና ችግር ሲገጥማቸውም የግል ሕክምና ድረስ እየተከፈለላቸው እንደሚታከሙ ገልፀው፤ መንፈሳዊ ሕይወታቸውም ቢሆን ግቢው ውስጥ ለሙስሊሞች፣ ለኦርቶዶክሶች እና ለፕሮቴስታንት ተከታዮች የፀሎት ቦታ መኖሩን ይጠቅሳሉ፡፡ ማኅበሩ ላደረገው አስተዋፅዖ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# በሌማት ትሩፋት የተከፈተ እንጀራ

ስምስም መንግሥቱ

ጓደኛሞቹ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከፋ ዞን ፤ ጊምቦ ወረዳ ጎጀብ ቀበሌ ውስጥ ነው የሚኖሩት። ከትምህርታቸው ጎን ለጎን አንዱ ሽንኩርት በመነገድ ሌላው ደግሞ ልኳንዳ ቤት በመሥራት ኑሮአቸውን ይደጉማሉ። ከሚያገኙት ገቢም በየወሩ እቁብ ይጥላሉ። እቁብ ሲደርሳቸው ተጨማሪ ሥራ መፍጠር እንዳለባቸው ጓደኛሞቹ ይመክራሉ።

ገበያውን ሲያጠኑም ወተት ለተጠቃሚው ማቅረብ አዋጭ ሆኖ አገኙት። ወስነውም አንዲት ላም ከነጊደሯ ስድስት ሺ ብር ገዝተው ሥራ ጀመሩ። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥም ውጤት አገኙበት። ጠዋትና ማታ ታልቦ ለገበያ ከሚያቀርቡት ወተት ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ (9600) ብር አገኙ። በአንድ ላም የተገኘው ውጤት ወደ ሁለተኛ እቅድ አሸጋገራቸው።

ጓደኛሞቹ ከስድስት ዓመት በፊት ጀምረው ውጤታማ ያደረጋቸውን የወተት ልማት የላሞች ቁጥር በመጨመርና ሌሎች ጓደኞቻቸውንም በማሳተፍ የበለጠ ቢያጠናክሩት ትርፋማ እንደሚያደርጋቸው አቀዱ። እቅዳቸውንም ወደ ተግባር ለመቀየር በእንቅስቃሴ ላይ እያሉ በማህበር ተደራጅተው በመረጡት የሥራ መስክ ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ወጣቶች ለሥራ መነሻ ብድር ይመቻችላቸዋል የሚል ከሚኖሩበት ወረዳ መልካም ዜና ሰሙ። ለእቅዳቸው መሳካት መልካም አጋጣሚ ሆነላቸው።

ብድሩን ያመቻቸላቸው አ ማይክሮ ፋይናንስ የተባለ አበዳሪ ድርጅት ሲሆን፣ 74ሺ ብር ብድር ፈቅዶላቸው እቅዳቸውን ወደ መተግበር ሥራ ገቡ። በሁለት ጓደኛሞች የተጀመረው የወተት ልማት ሥራ አራት አባላትን አፍርቶ ወደ ኢንተርፕራይዝ ከፍ አለ። በየጊዜው ለውጥ እያስመዘገቡ፣ ወደ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር ሩቅ አልመው መጓዝ ጀመሩ።


እኛም የአካባቢያቸውን ፀጋ ለይተው እየተጠቀሙበት ያሉትን የነዚህን ባለራዕይ ወጣቶች የሥራ እንቅስቃሴ በሥፍራው ተገኝተን ለማየት እድሉን አግኝተናል። መነሻ ሃሳቡን ከማፍለቅ ጀምሮ ኢንተርፕራይዙንም በመምራት እስካሁን በሥራው ውስጥ ከሚገኘው ወጣት በረከት ደገፉ ጋር ነበር ቆይታ ያደረግነው። ለኢንተርፕራይዛቸውም መጠሪያ «ኑኒ ከፊቾ» የሚል ስያሜ ሰጥተውታል። ስያሜው ወደ አማርኛ ሲመለስ «እኛ የከፋ ልጆች» ማለት እንደሆነም ወጣት በረከት ነግሮናል።

ወጣት በረከት እንደገለጸልን፤ ከጓደኛው ጋር ሆነው የጀመሩትን ሥራ ለማሳደግ ሁለት አባላትን ጨምረው አራት በመሆን ወደ ኢንተርፕራይዝ የተሸጋገሩ ቢሆንም አንዱ አባላቸው በሞት ስለተለያቸው ቀሪዎቹ ናቸው ሥራውን የቀጠሉት። ከአባላቱ መካከልም አንድ ሴት ትገኛለች። ኢንተርፕራይዙ ከአ ማይክሮ ፋይናንስ አበዳሪ ድርጅት ባገኘው ብድርም ሶስት የወተት ላሞች ከነጥጃቻቸው ገዝቶ ሥራውን ያሰፋ ሲሆን፣ የወጣቶቹን ትጋት የተገነዘቡ የአባላቱ ቤተሰቦች ደግሞ ለሥራ የሚሆን ቦታ በመስጠት ትብብራቸውን አሳይተዋል። የአካባቢው ማህበረሰብ የአገዳና የሩዝ ተረፈ ምርት መኖ በመስጠትም አበረታትቷል። ለዚህም አባላቱ ትልቅ ምስጋና አላቸው።

ላሞቹ ያለ ማቋረጥ ለስድስት ወር ያህል ነበር የታለቡት። ተሽጦ ከሚገኘው ገቢም ተጠራቅሞ ለከብቶቹ በረት (ማደሪያ) ተሰራ። ላሞቹ ሲነጥፉም ተሸጠው ተጨማሪ ገበያ አስገኝተዋል። በአሁኑ ጊዜም የወተት ምርታማነትን በመጨመር ገቢን ለማሳደግ በተሻሻሉ ዝርያዎች ለመተካት ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆኑ ነው ወጣት በረከት የነገረን።

እንደ ወጣት በረከት ገለጻ፤ ላሞቹ ሲነጥፉ ከሥር ከሥር እየተሸጡ በመሆኑ ቁጥራቸው በየጊዜው ይለያያል። አሁን ላይ 14 የወተት ላሞች ናቸው ያሉት። የኢንተርፕራይዙ አባላት እንደ ሀብት (ካፒታል) የሚቆጥሩት ያሏቸውን ከብቶች፣የሰሩትን በረት፣ እስከዛሬ ባገኙት ገቢ በኑሮአቸው ላይ ያመጡትን ለውጥ ጭምር ነው።

እያንዳንዱ አባል፣ የራሱን መኖሪያ ቤት ሰርቷል። ቤተሰብም መሥርቶ እየመራ ይገኛል።



ይሄ ለአባላቱ ትልቅ ለውጥ ነው። ወጣት በረከት «ሁላችንም የኢተርፕራይዙ አባላት አንድ እርምጃ ተራምደናል» ሲል ነው ስኬታማነታቸውን የገለፀው። ለኢንተርፕራይዙ ህልውና የሚሆን በባንክ መጠነኛ ቁጠባ መኖሩንም ነግሮናል።

በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው በዚህ ሥራ ውስጥ ባይሆኑ ኖሮ እጣ ፈንታቸው ለቤተሰብ ሸክም መሆን፣ አልባሌ ቦታም የሚውሉበት አጋጣሚ ይፈጠር እንደነበር ነው ወጣት በረከት ያጫወተን። ሥራው ጥንካሬንና ትዕግሥትንም እንደሚጠይቅ ይገልጻል። «ውጤት የሚገኘው በሂደት ነው። ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች ያጋጥማሉ። በትዕግሥት ከታለፈ ግን ውጤት ይገኛል። ውጤቱን እያዩ ሲሄዱ ደግሞ የመሥራት ፍላጎት ይጨምራል። በዚህ መንገድ ውስጥ አልፈን ነው በሥራው ላይ የቆየነው» ሲልም የሥራ ቆይታቸውን አጫውቶናል። ኢንተርፕራይዙ የራሱን አባላት ብቻ ሳይሆን፣ ለስድስት ወጣቶችም የሥራ እድል በመፍጠር አስተዋጽኦ ማበርከቱንም አመልክቷል።

ከብቶችን የሚያጠቃ ገንዲ የተባለ ዝንብ በአካባቢው ላይ በስፋት መኖሩን የገለፀልን ወጣት በረከት፤ የእንስሳቱን ጤና መጠበቅ ወሳኝ እንደሆነም ይገልጻል። በዚህ በኩል ወረዳው በከፍተኛ ሁኔታ እገዛ እያደረገላቸው እንደሆነ ነው የነገረን። ለገንዲ ዝንብ መከላከያ የሚሆን መድኃኒትና ህክምና በነፃ እንዲያገኙ እንዳመቻቸላቸውና ይህም ከፍተኛ ድጋፍ እንደሆናቸው ነው የገለጹልን። የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ከብቶችን የሚያገኙበት መንገድ ወረዳው እያመቻቸላቸው መሆኑን ነግሮናል። እርሱ እንዳለው አካባቢው ላይ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ከብቶችን የመጠቀም ልምድ ባለመኖሩ በወተት ላምም ሆነ በሥጋ ምርታማነት ላይ መቀነስ ይስተዋላል።

ምርታማነታቸውን ለማሳደግ በወረዳው በኩል እየተፈጠረላቸው ያለው ምቹ ሁኔታ የበለጠ እንዲሰሩና ወደፊት ወደ ኢንዱስትሪ የማሳደግ እቅዳቸውን ለማሳካት ጉልበት እንደሚሆናቸው የሚናገረው ወጣት በረከት፤ ከወተት ምርት በተጨማሪ የሥጋ ከብቶችንም በማቅረብ፣ ንብ በማነብ ሥራቸውን የማስፋት፣ አቅርቦቱን በኢንዱስትሪ ደረጃ በማሳደግ የዓለም ገበያ ውስጥ መግባት፣ በሥራቸውም ከአካባቢያቸው አልፈው የሀገራቸውንም ስም ለማስጠራት ሰፊ እቅድ ይዘው እየሰሩ እንደሆነ ነው የገለፀው።

መንግሥት በሌማት ቱሩፋት በግብርናው ዘርፍ በእንስሳትና ወተት ልማት፣ በንብ ማነብ፣ በዓሣ ልማት፣ የሰጠውን ትኩረት ለመጠቀም መልካም አጋጣሚ እንደሆነም ያስረዳል።

በተለያየ ምክንያት ሥራ መፍጠር ያልቻሉ ወጣቶች ከእነርሱ ኢንተርፕራይዝ ምን ተሞክሮ ማግኘት ይችላሉ ብለን ላቀረብንለት ጥያቄ ወጣት በረከት የሚከተለውን መልሶልናል። «በአካልም በስልክም የሚጠይቁት ወጣቶች መኖራቸውንና አንድ ሥራ ሲጀመር ስኬት ብቻ ሳይሆን፣ ውጣ ውረዱንም ለመቋቋም በሥነ ልቦና ዝግጁ መሆን እንደሚያስፈልግ፣ ሥራ ለመጀመርም መፍራት እንደሌለባቸው፣ ውጤት ከመውደቅ መነሳት የሚገኝ መሆኑን ገልጾልናል። » በተለይ ደግሞ እነርሱ ያሳለፏቸው ችግሮች እንዳይገጥሟቸው በቀላሉ ለስኬት የሚበቁበትን መንገድ በማሳየት ምክሩን እንደሚለግሳቸውም ነው የገለፀው።

የሚሰሩ እጆች በሚያስፈልጉበት በዚህ ወቅት ሥራ ለመሥራት ጥረት ለማያደርጉ ወጣቶችም ወጣት በረከት መልዕክት አለው። «ሥራ መሥራት ለመንፈስ እርካታ፣ ለአካልም ጥንካሬ ነው። አንድ ሰው በዚህ ምድር ላይ ሲኖር በሚችለው ሁሉ ለሀገሩ አንድ ነገር ስርቶ ማለፍ ይኖርበታል።


ይህን ሳይገነዘቡ ሀገርንና ሕዝብን በሚጎዳ ተግባር የሚሰለፉ ወጣቶች ቆም ብለው ያስቡ ነው የምለው። ከጥፋት ሳይሆን ከልማት ነው ትርፍ የሚገኘው። ጊዜን በሥራ ከማሳለፍ ይልቅ አልባሌ ቦታ ላይ መዋልን የሚመርጡ ወጣቶች መኖራቸውን በአካበቢዬም እታዘባለሁ። በምክር ለመመለስ ጥረት አደርጋለሁ። ግን የብዙዎች ትብብር ነው የሚያስፈልገው።

እባካችሁ ወጣቶች እንስራ ነው የምለው። ወላጆቻችን ብዙ መሬት ኖሯቸው ግን እንዴት ምርታማ መሆን እንደሚችሉ በቴክኖሎጂ ባለመታገዛቸው በግብርናው ዘርፍ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልቻሉም። ኑሮአቸውም አልተለወጠም። እኛም እነርሱ ባለፉበት መንገድ ሳይሆን ግብርናውን በማዘመን ለለውጥ መነሳት ይኖርብናል። እኛ ለመሥራት ፍላጎቱ ካለን ለማደግ እድሉ አለን። እንጠቀምበት ነው የምለው» ሲልም መልዕክቱን አስተላልፏል።

እንዲህ በትጋት እየሰሩ ላሉ ኢንተርፕራይዞች ክልሉ እያደረገላቸው ስላለው እገዛና ድጋፍ በከፋ ዞን ጊምቦ ወረዳ ሥራ ክህሎትና ገበያ ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ዘውዴ እንደገለጹልን፤ በክልሉ በማህበር ተደራጅተው ወደ ሥራ ለሚገቡ ወጣቶች በግብርና፣ በአገልግሎት፣ በግንባታና በሌሎችም በመረጡት ዘርፎች የሥራ ዕድል ተመቻችቶላቸዋል።

በወረዳው በሚገኙ 30 የገጠር ቀበሌዎችና አምስት ማዘጋጃ ቤቶች ከሶስት መቶ በላይ የሚሆኑ በተለያየ የሥራ ዘርፍ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች መኖራቸውንና እያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝም በቁጥር የተለያየ አባል ይዞ እንደሚንቀሳቀስ የጠቆሙት አቶ ጌታቸው፤ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ሰፊ ቁጥር ላላቸው ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን አመልክተዋል። ጎጀብ በማዘጋጃ ቤት ሥር ከሚገኙ አምስቱ መካከል አንዱ መሆኑንና ሰፊ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች የሚገኙበት አካባቢ እንደሆነም አመልክተዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ በጎጀብ ብቻ በከተማ ግብርና የተሰማሩ 28፣በማኑፋክቸሪንግ 3፣ በአገልግሎት 22 ኢንተርፕራይዞች ይገኛሉ። ይህን ያህል ኢንተርፕራይዝ ማፍራት የተቻለው ማዘጋጃ ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀሱና የወጣቶች



ወጣት በረከት ደገፋ፣

የሥራ ተነሳሽነት በመጨመሩ ነው። በወተት ልማት ተሰማርተው ውጤታማ የሆኑት «ኑኒ ከፊቾ» ኢንተርፕራይዝም የዚሁ አካባቢ ናቸው። ኢንተርፕራይዙ በሥራም ሆነ የተበደረውን ፈጥኖ በመመለስ በአርአያነት ይጠቀሳል። ተጨማሪ ብድር በማመቻቸትና የተለያዩ እገዛዎችንም እንዲያገኙ በማድረግ ኢንተርፕራይዞቹን ማበረታታት ያስፈልጋል። ወረዳው በሚችለው ሁሉ እያገዛቸው ይገኛል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ የድጋፍ ማዕቀፎችን ለይቶ በተሻለ እንቅስቃሴ ውጤታማ የሆኑትን ማበረታታት፣ ወደኋላ የቀሩትንም ክፍተቶቻቸውን ፈትሾ ማብቃት ያስፈልጋል። እየተሰራ ያለውም በዚህ መንገድ ነው። «ኑኒ ከፊቾ» ኢንተርፕራይዝ የመሥሪያ ቦታ ችግር ነበረበት። አባላቱ ቤተሰብ በሰጣቸው ቦታ ላይ ነው እየሰሩ ውጤታማ የሆኑት። ይህን ጥረታቸውን በማየት ወረዳውና ማዘጋጃ ቤቱ በጋራ ተነጋግረው አሁን ላይ ለበረት የሚሆንና የግጦሽ ቦታ እንዲሰጣቸው አድርገዋል። ለአካባቢው ወጣቶች አርአያ በመሆኑም በተለያየ መንገድ ድጋፍ እየተደረገለት ነው።

የኢንተርፕራይዙን እንቅስቃሴ የሚያዩ የአካባቢው ወጣቶች ለሥራ እየተነሳሱ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ጌታቸው፤ ጎጀብ ውሽውሽ ከተማ ላይ በወተት ላም ልማት ወጣቶች ተደራጅተው ሥራ መጀመራቸውንና በተቀሩት ጊምቦ ወረዳ አካባቢዎችም በንብ ማነብ፣ ዳቦ ቤት በመክፈት ውጤታማ ሆነው በአርአያነት የሚጠቀሱ መኖራቸውን አመልክተዋል።

ወጣቶቹ በወተት፣ በማር፣ በዳቦ አቅርቦቶች ነዋሪውንም ተጠቃሚ ማድረጋቸው ሌላው በመልካም ጎን የሚጠቀስ እንደሆነም ገልጸዋል። በዓሣ ልማትም ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ መኖሩን አመልክተዋል። በገበያ ትስስር በኩልም በአካባቢው ላሉ ትላልቅ የእርሻ ድርጅቶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በማቅረብ ተጠቃሚ የሚሆኑበት እድል መኖሩንም አመልክተዋል።

ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ መሆኑ ግንዛቤ ተይዞ ተሞክሮው ሰፍቶ የበለጠ ውጤት እንዲመዘገብ ማገዝ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ጌታቸው የመንግሥት ድጋፍና ክትትል ብቻውን በቂ እንዳልሆነና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላትም በትብብር ቢሰሩ በሀገ። ደረጃ ትልቅ ስኬት ማስመዝገብ እንደሚቻል ገልጸዋል። እየተሰራ ያለው ሥራ ኢንተርፕራይዞቹ በድጋፍ ብቻ እንዲቀጥሉ ሳይሆን፣ ሀብት አፍርተው ለሌሎችም የሥራ እድል መፍጠር እንዲችሉ፣ በሀገር ኢኮኖሚ እድገትም አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ማስቻልም ጭምር እንደሆነ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል ብለዋል።

ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ መታረም አለበት ያሉትንም አቶ ጌታቸው እንዲህ አንስተዋል። ለሥራ የተበደሩት ብድር ተመላሽ ሲሆን፣ መልሶ አዲስ ለሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች መዋል ሲኖርበት ለመደበኛ የብድር አገልግሎት ተግባር ይውላል። ይሄ ደግሞ ሥራ በሚፈጠርላቸው ወጣቶች ላይ መጉላላት እያስከተለ ነው። ገንዘቡ በሥራ እድል ፈጠራ አካውንት (ማጠራቀሚያ ሂሣብ) ውስጥ ነው መቀመጥ ያለበት።

አንዳንዶቹ ግንዛቤ በመፍጠር የሚፈቱ በመሆናቸው እንደ ችግር ላይነሱ ይችላሉ። ክትትልና ድጋፍን አጠናክሮ መቀጠል ከተቻለ የወጣቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሚቻልም አቶ ጌታቸው ተናግረዋል።

# የኮርፖሬሽኑ ተስፋ ሰጪ የከበሩ ማዕድናት እሴት መጨመር ሥራዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ የበርካታ የከበሩ ማዕድናት መገኛ ናት። በዓለም በእጅጉ ከሚታወቁና ተፈላጊ ከሆኑት እንደ ሳፋየር፣ ኤምራልድ፣ ኦፓል፣ ጃስበር፣ ኦብሲዲያን፣ ጋርኔት፣ አሜቲስት እና ሲትሪን ከመሳሰሉት የከበሩ ማዕድናት ከ40 በላይ የሚሆኑትም ይገኙባታል፡፡ ለማዕድናቱ ትኩረት ሳይሰጥ ከመቆየቱ ጋር በተያያዘ እነዚህን ማዕድናት አልምቶና እሴት ጨምሮ በሚገባ ተጠቃሚ መሆን ሳይቻል ቆይቷል፡፡ የከበሩ ማዕድናት ሀብቶችን በአግባቡ አውቆና አጥንቶ ጥቅም ላይ በማዋል በኩል ውስንነቶች እንደነበሩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ለአጠቃላይ የማዕድን ዘርፉ በመንግሥት በኩል ትኩረት የተሰጠው መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም ቢሆን ለወርቅና ሌሎች ማዕድናት የተሰጠውን ትኩረት ያህል ለከበሩ ማዕድናት ትኩረት አልተሰጠም ነበር ሲሉ የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለከበሩ ማዕድናትም ትኩረት መስጠት መጀመሩን እነዚሁ ባለሙያዎች ጠቅሰው፣ ይህን ተከትሎ በከበሩ ማዕድናት ልማትና ግብይት ላይ መነቃቃት እየተፈጠረና ለውጦች እየተስተዋሉ መምጣታቸውንም ያመላክታሉ፡፡

እንደ ሀገር በከበሩ ማዕድናት ዘርፍ ኢትዮጵያ ያላትን ያልተነካ ሀብት በማውጣትና እሴት በመጨመር ለዓለም በማስተዋወቅ ረገድ ሰፋፊ ሥራዎችን መሥራት እንደሚጠይቅ ይታመናል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተፈጠረውን መነቃቃት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በግልም ሆነ በመንግሥት ደረጃ በከበሩ ማዕድናት ልማትና እሴት ጭመራ ላይ ተሰማርተው የሚሰሩ ተቋማት እየታዩ ናቸው፡፡


ከእነዚህ መካከል የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን አንዱ ነው፡፡ ኮርፖሬሽኑ በከበሩ ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር፣ ከዘመኑ ጋር አብረው የሚሄዱ ዲጂታል ፕላትፎርሞችን በመጠቀም የከበሩ ማዕድናትን በዓለም ገበያ እያስተዋወቀና እየሸጠ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት እየሰራ መሆኑን ይገልጻል፡፡

የኮርፖሬሽኑ የጌጣጌጥ ማዕድናት ማምረቻ ክፍል ሥራ አስኪያጅ አቶ ዘካሪያስ ፍቃድ እንደሚሉት፤ እንደ ሀገር በማዕድን ዘርፍ ላይ በትኩረት ሲሰራ የቆየው ለኢንዱስትሪ ግብዓት በሚውሉ ማዕድናት እንዲሁም በወርቅ እና ተዛማጅ ማዕድናት ላይ ነው፡፡ በከበሩ ማዕድናት ላይ በትኩረት መሥራት የተጀመረው ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው፡፡

የከበሩ ማዕድናት ቢሰራባቸው ለሀገር ትልቅ የገቢ ምንጭ ማስገኘት እንደሚችሉ ሥራ አስኪያጁ ጠቅሰው፣ ማዕድናቱ አላቂ የማዕድን ሀብት መሆናቸው ታሳቢ ተደርጎ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግ እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል፡፡

አቶ ዘካርያስ እንደሚሉት፤ ኮርፖሬሽኑ ከአመራረት ጀምሮ ያሉ ሂደቶች በሚገባ እንዲስተካከሉ ለማድረግ ከክልሎች ጋር በመሆን በሙያ የታገዙ ሥራዎች እንዲሰሩ ጥረቶች እያደረገ ይገኛል፡፡ ማዕድኑ በአብዛኛው ወደ ውጭ ሲላክ የኖረው በጥሬው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደ ሀገር ትልቅ ኪሳራ ሲደርስ ቆይቷል፡፡ ማዕድናቱን እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ ማቅረብ ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ እሴት መጨመር ሲባል በአጠቃላይ በተፈጥሮ የተገኘው ማዕድን ውበት እንዲላበስ የሚደረግበት መንገድ ነው።

ኮርፖሬሽኑ በአሁኑ ወቅት እሴት መጨመር ላይ በስፋት እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በእሴት ማዕከሉ ሥራ የከበሩ ማዕድናቱ ከወርቅ እና ከብር ጋር ወደ ለጌጣጌጥነት ከመዋላቸው በፊት ያለው ሥራ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡ የከበሩ ማዕድናት ከሚያመርቱ የክልል የከበሩ ማዕድናት አምራች ማህበራት ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር የከበሩ ማዕድናት በጥሬው እንደሚገዛ ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ማህበራት በሕጋዊ መልኩ የተደራጁ ሕጋዊ እውቅና ያላቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ኮርፖሬሽኑ በጥሬው በገዛቸው በእነዚህ ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ እንደሚያቀርብ ተናግረዋል፡፡



እሳቸው እንዳሉት፤ ቀደም ሲል የከበሩ ማዕድናቱ ምንም ዓይነት እሴት ሳይታከልባቸው በጥሬው ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ ይደረግ ነበር፡፡ ማዕድኑ በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር አልፎ ውጭ ሀገር የሚወሰድበት ሁኔታ እንዳለም ገልጸዋል፡፡

ማዕድኑ በጥሬ መላኩ ሳያንስ በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር እንዲወጣ መደረጉ እንደ ሀገር ኪሳራ ሲያስከትል ቆይቷል ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ይናገራሉ። አሁን መንግሥት ይህን ሕገ ወጥነት ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን ጠቅሰው፣ ቁጥጥሩ በደንብ እየተጠናከረ የመጣበት ሁኔታ እንዳለም ያመላክታሉ፡፡

ሥራ አስኪያጁ ኮርፖሬሽኑ በከበሩ ማዕድናት ላይ እሴት የመጨመሩን ሥራ አጠናክሮ መቀጠሉን ጠቅሰው፣ ዘንድሮ የጌጣጌጥ ማዕድናት ሥራ ወርክሾፕ ለማቋቋም አቅዶ እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡ የጌጣጌጥ ሥራ ማለት በወርክሾፑ የሚመረቱ ማዕድናትን ከወርቅ፣ ከብር እና ከሌሎች ነገሮች በማምረት ለአንገት፣ ለጆሮ፣ ለእጅ እና ለመሳሰሉት ጌጣጌጥነት ሙሉ ለሙሉ እንዲውሉ የሚደረግበት መሆኑን ያብራራሉ፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ይህን ለማድረግ ወርክሾፕ ያስፈልጋል፡፡ ወርክሾፑ እስከሚቋቋም ድረስም እሴት የመጨመር ሥራው እየተሰራ ነው። በወርቅና በብር ሥራ ላይ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር በሕጋዊ መንገድ የወርቅና የብር ጌጣጌጥ የማስዋቡ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡ ኮርፖሬሽኑ በዚህ መልኩ እሴት የመጨመሩን ሥራ በማስፋፋት ሌሎችም ወደ ሕጋዊ መንገድ እንዲመጡ እያደረገ ይገኛል፡፡

በሀገሪቱ ከ40 በላይ የከበሩ ማዕድናት ዓይነቶች ይገኛሉ፡፡ ምን ያህሉ ላይ በሚገባ ተሰርቷል የሚለው ግን በደንብ መታየትና መለየት ይኖርበታል፡፡ ዋንኛው ነገር እሴት መጨመሩ ላይ መሥራት ነው፤ ከዚህ ጎን ለጎን በማዕድን ልማቱ ላይ ትኩረት በመስጠት የአምራቾቹን አቅም ማሳደግና ባለሙያ ማፍራት ላይ ሊሰራበት ይገባል፡፡ በዚህም ላይ በሀገር ደረጃ ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመነጋጋር ሥራዎች የተጀመሩበት ሁኔታ እንዳለም ሥራ አስኪያጁ አመላክተዋል፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ኮርፖሬሽኑ ምርቶቹን የሚሸጥባቸው ቦታዎችም አሉት፡፡ አንደኛው መሸጫ በኮርፖሬሽኑ ግቢ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የመንገደኞች ተርሚናል ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህም ማዕድናትን ከማስተዋወቅ እንዲሁም ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችል ግንዛቤ ለመፍጠርና በኢትዮጵያ ያሉ ማዕድናትን ለማስተዋወቅ ያግዛል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም ሌሎች ተጨማሪ የመሸጫ ቦታዎች በመክፈትና ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸጥ እየተሰራ ነው፡፡

አሁን የከበሩ ማዕድናት ዘርፍ እንደ አዲስ እየተነቃቃ መሆኑን አመልክተው፣ የከበሩ ማዕድናትን ለማስተዋወቅ እንዲሁም የዲጂታል ገበያ ተደራሽነትን ለማስፋት የሚያስችሉ ሥራዎችም እየተሰሩ ይገኛሉ። በቅርቡ በኢትዮጵያ ዲጂታል ማርኬቲንግ ላይ ለመግባት ኤግል ላይን ከሚባል ድርጅት ጋር በመተባበር ‹ኢትዮጵያንስ ሚኒራል› የሚል የዲጂታል መገበያያ ፕላትፎርም ተዘጋጅቶ ይፋ ሆናል፡፡ የዚህ ዋና ዓላማም በኦንላይን መንገድ ግብይት መፈጸም ነው፡፡ ይህም በአሊባባ እና አማዞን ደረጃ ምርቶቹን ለማስተዋወቅ የሚያስችል ሥራን ለመሥራት ፡፡

የክፍያ ሥርዓቱንም ለማቀላጠፍ ከዳሽን ባንክ ጋር እየተሰራ ሲሆን፣ በኦንላይን መክፈል የሚቻልበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ከማስተር ካርድ ጋርም እንዲሁ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

ግብዓቱ ሕጋዊ መንገድን ተከትሎ በኦንላይን እንዲሆን ቢደረግም ማዕድናቱ እንደ ማንኛውም እቃ በሕገ ወጥ መንገድ የሚወጡበት ሁኔታ እንዳለ አመልክተው፣ ምርቶቹ ሕጋዊነትን በጠበቀ መልኩ ለደንበኞች እንዲደርሱ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ፖስታ ድርጅት ጋርም እየተሰራ መሆኑን ያስታወቁት፡፡

አሁን ገበያው ላይ የተወሰነ መቀዛቀዝ እንዳለም አቶ ዘካርያስ ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ዋናው ምክንያትነት የማዕድናት ሕገ ወጥ ግብይት መሆኑን ተናግረው፣ ሕገ ወጥ የማዕድናት ግብይቱን ለመቆጣጠር ከብሔራዊ ደህንነት ጋር የሚከናወኑ ተግባሮች ተጠናክረው መቀጠላቸውን አስታውቀዋል፡፡

የኮርፖሬሽኑ ምርቶች ፎቶ "ኢትዮጵያ ሚኒራል ዶት ኮም" ላይ መለቀቁን ጠቅሰው፣ ይህም ማንኛውም ደንበኛ ማዕድናቱን ለመግዛት ሲፈልግ ወደ ዌብሳይቱ ገብቶ በኦንላይን እንዲያዝ የሚያስችል መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡ ደንበኛው የሚፈልገውን ምርት ካዘዘ በኋላ ክፍያውንም በተቀመጡት አማራጮች ተጠቅሞ በመክፈል በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት አማካኝነት ንብረቱን መረከብ የሚችልበት አሰራር መዘርጋቱን አስታውቀዋል፡፡

የኦንላይን ገበያ እምብዛም ያልተለመደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጥርጣሬዎች መኖራቸው ግብይቱ በሚፈለገው ልክ እንዳይሄድ የሚያደርግ ተግዳሮት እንደነበር ሥራ አስኪያጁ አስታውሰው፣ ይህንን የኦንላይን ሥርዓት ለማጠናከርና እንደ ሀገር ለማስፋት ሌሎች የከበሩ ማዕድን ላኪዎችም እንዲሳተፉበት ክፍት መደረጉን ገልጸዋል፡፡ እስካሁንም ብዙ ላኪዎች መመዝገባቸውንና ሁሉንም በማሳተፍ በጋራ እየተሰራ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ ይህም አሰራር አንደኛ ማዕድናቱ በሕጋዊ መንገድ እንዲሸጡ ለማድረግ እንደሚረዳ ገልጸው፣ ሁለተኛ ማዕድናቱ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲመረቱና ለደንበኞች እንዲደርሱ የሚያስችል መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ እንዳሉት፤ ኮርፖሬሽኑ ምርቶቹን በዲጂታል ገበያ ለማቅረብ የሚያስችሉ በቂ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡ አሁን በቂ የምርት ክምችትም አለው። ለምሳሌ ያለውን ክምችት ለማሳየት ያህል ጌጣጌጦችን ለሚሰሩ ድርጅቶች አንድ ጊዜ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከአንድ ሺ እስከ ሁለት ሺ ነው፡፡ የገበያው ተደራሽነት እየሰፋ ሲሄድ ከዚህ በላይ ማምረት ስለሚያስፈልግ የማምረት ሥራውን ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ የተለያዩ ማዕድናትን በተለያዩ ዲዛይኖች በዓይነትም ሆነ በብዛት አምርቶ ለገበያ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ እንደ ደንበኛው ፍላጎት ምርቶቹን ለማቅረብ ኮርፖሬሽኑ ሁሉም ማዕድናት ላይ ትኩረት አድርጎ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የከበሩ ማዕድናትን በጥሬ ለገበያ ማቅረብ የሚበረታታ እንዳልሆነም ጠቅሰው፣ በጥሬው ለገበያ ማቅረብ ይህ እንደ ቢዝነስ አዋጭ ሳይሆን አክሳሪ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ይህንንም ምሳሌ ጠቅሰው ሲያብራሩ «አንድ ማዕድን በግራም 50 ሺ ብር መሸጥ እየተቻለ አምስትና ስድስት ሺ ብር መሸጥ ትክክል አይደለም» ይላሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ አንድ ማዕድን እሴት ሲታከልበት እና ሳይታከልበት ያለው የገበያ ልዩነት ሰፊ ነው፡፡ ኮርፖሬሽኑ በተያዘው በጀት ዓመት እሴት የመጨመሩን ሥራ አጠናክሮ ለመቀጠል አቅዶ እየሰራ ነው፡፡ የማዕድናቱን ደህንነት በማስጠበቅ ረገድም በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡

ኮርፖሬሽኑ በተያዘው ዓመት አንዱ ስትራቴጂ አድርጎ እየሰራ ያለው ሥራ የማዕድን ልየታ ላብራቶሪ ማቋቋም መሆኑንም ሥራ አስኪያጁ ጠቁመዋል። በአሁኑ ወቅት 80 በመቶ ያህል የመመርመሪያ መሳሪያዎች እንዳሉት ተናግረው፣ ቀሪዎቹን ጥቂት መሳሪያዎች ከውጭ በማስገባት ዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው የአይኤስኦ ሰርተፊኬትን በመውሰድ ለሁሉም አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎት ለመስጠት ይሰራል ብለዋል፡፡ በከበሩ ማዕድናት ዘርፍ ብዙ ፍላጎት እንዳለም ጠቅሰው፣ ሰው ግንዛቤው ኖሮት ማዕድኑን እንዲገዛ ለማድረግ ስልጠናው በመስጠት የባለሙያ ክፍተቶች የመሟላት ሥራዎች እንደሚሰሩ አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ ዘካርያስ ገለጻ፤ በከበሩ ማዕድናት ዘርፍ ከአመራረቱ ጀምሮ ለፍጻሜ እስከሚደርስ ያለውን ሂደት በተመለከተ እውቀት የሚያስጨብጥበት የጀኦሞሎጂ ትምህርት ቤት ለማቋቋም የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡ ትምህርቱን ለመማርና ስልጠና ለመወሰድ ብዙዎች ጥያቄ እያቀረቡ መሆናቸውን ተከትሎ ያለውን የመማር ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ በቅርቡ አጫጭር ስልጠናዎች መስጠት ተጀምሯል። በመጀመሪያ ዙር ስልጠናም ከ30 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ስልጠናውን ወስደዋል፡፡ ስልጠናው ስለማዕድናት አጠቃላይ ግንዛቤን የሚያገኙበት የተሻለ አረዳድ እንዲኖራቸው ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ በ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት እሴት በመጨመር የጌጣጌጥ ማዕድናትን ለማምረት ከተያዘው እቅድ ከ85 ከመቶ በላይ የሚሆነውን መፈጸም ተችሏል፡፡ የእቅዱ መቶ በመቶ እንዳይሳካ ካደረጉ ዋንኛ ምክንያቶች መካከል የኃይል መቆራረጥ እና ማዕድናቱ በሚመጡባቸው የተለያዩ አካባቢዎች የታዩ የጸጥታ ችግሮች ናቸው፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማትና ከጸጥታ አካላት ጋር እየተሰራ ነው፡፡

የማዕድናት ልየታ ላብራቶሪም የሚቋቋም ይሆናል። የጌጣጌጥ ወርክሾፑንም በማቋቋም ሙሉ በሙሉ የወርቅና የብር ማስጌጥ ሥራው በውስጥ አቅም እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ለጌጣጌጥ ማዕድናት መቆረጥና ማለስለስ /የላፒደሪ/ ወርክሾፑ ባለሙያዎችንም ሆነ መሳሪያዎችን በመጨመር አቅሙን የማሳደግና ማጠናከር ሥራ ማካሄድ እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል። ለእዚህም ባለሙያዎች የመቅጠሩ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## እፎይ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ለምን እንደሆነ አላውቅም አራት ሰዓት አለፍ ሲል ይደብተኛል፡፡ ድብርቴን የምሸሸው የሆረር ፊልም በማየትና በደረቴ በመተኛት ነው፡፡ የዛሬውም አራት ሰዓት እንደተለመደው ምርግ ነበር፡፡ አብሮኝ ከሚኖረው ፊታወቅ ጋር አዋተን በገዛናት ፍራሽ ላይ በደረቴ ተኝቼ የረፋድ ድብርቴን አጎንብሼ አሳልፋለሁ፡፡ በጣቴ መሬት እየጫርኩ የማላውቀውን ነገር ሚዲያው ላይ እጽፋለሁ። በዚህ መሐል ስሜን ከውጪ ሲጠራ ሰማሁት..ሮቤል? አንተ ሮቤል?

ነፍሴ ሳቀች..ጀምበር ፈንጥቃ ስፍራዋን ለረፋድ ስትለቅ ማንም የማያስቀኝ ሰው ነበርኩ፡፡ ከሰዓት እስኪሆን ማለዳ በጉያው ውስጥ የሸሸገው የአራት ሰዓት አጋንንት ከላዬ ላይ ጮሆ እስኪወጣ ድረስ ማንም የማያዝናናኝ ሰው ነበርኩ፡፡ ለዘመናት የተላመድኩት ድባቴዬ የት እንደገባ ሳላውቀው በሄመን ድምፅ ነቃሁ። ‹ሮቤል..አንተ ሮቤል? ድምፅዋ ወዳለሁበት እየቀረበ መጣ፡፡ ከአልጋዬ ላይ እንዴት እንደተፈናጠርኩ አላውቅም ራሴን በሩ ላይ አገኘሁት። እኔ ስወጣ እሷ ስትገባ ተጋጨን፡፡ መቼም የማይደገም ግጭት። አይኖቼን የት ላድርጋቸው? አፈርኳት፡፡ ፊት ለፊቴ በግንባሬ የተገጨ ግንባሯን እያሻሸች ቆማለች። ዓይኖቿ የእፍረት ዝናር ታጥቀው ያዩኛል፡፡ ጡቶቿ በስስ የቤት ውስጥ ፒጃማ ተወድረው ደረቴ ላይ ተነጣጥረዋል። ከንፈሯ ሩብ ያህሉ በጥርሶቿ በቁንጥ ተነክሶ ተደቅኖብኛል፡፡ አይኖቼን የት ላድርጋቸው?

መደናበሬን አይታ ይሆን እንጃ ‹ቤት ማንም የለም ናና ተጫወት› ብላኝ ወደ ቤት ተመለሰች፡፡

ከበሩ ላይ አልተንቀሳቀስኩም፡፡ ፊልም የሚመስ ለውን አጋጣሚ በአዕምሮዬ እየመለስኩ ቆሜአለሁ። ቆይቼ ሳስበው ከመጋጨትም በላይ የሆነ ነገር ያስተናገድን ይመስለኛል፡፡ ደረቴ ላይ አሁንም ድረስ የሚሰማኝ ደስ የሚል የውጋት ሕመም አለ..በጡቶቿ የተወጋሁት፡፡ ጉንጬ ላይ ፀጉሯ የገረፈኝ አንዳች የሚያክል ሰንበር አለ፡፡ ራሴን በመስተዋት ሳየው ቀይ የከንፈር ቀለም ከንፈሬ ላይ ተለጉዶ ነበር፡፡ ይሄ እንዴት ሆነ? ደስ የሚል የሚያሳፍር ሳቅ ሳኩኝ፡፡ ሰው እንዴት በአንድ ጊዜ ደስ የሚልና የሚያሳፍር ሳቅ ይስቃል? ሄመንን አፈርኳት፡፡ መንገድ ላይ ስንገናኝ ለመሳሳም የተቀጣጠርን እንጂ ለመጋጨት የተገናኘን አንመስልም ነበር፡፡

አንዳንድ ቀኖች አሉ..የሰው ልጅ አስቦና ተዘጋጅቶ የማይደግማቸው፡፡ አንዳንድ አጋጣሚዎች አሉ እንዴት እንደመጡ፣ እንዴት እንደሆኑ ታስቦ የማይደረስባቸው። ከሄመን ጋር የተጋጨንበትን የዛሬውን ቀን ጻፍኩት፡፡ መቼም እንዳይረሳኝ ስለምፈልግ፡፡

እፎይ ብያለሁ..መቼም እንደዛሬ እፎይ ብዬ አላውቅም፡፡ አንዳንድ ድምፆች አሉ ከሕይወት እስራት፣ ከመኖር ስብራት ነፃ የሚያወጡ፡፡ አንዳንድ አንደበቶች አሉ ከካህን አፍ ጥመው ለጆሮ የሚጣፍጡ፡፡ አንዳንድ ቀኖች አሉ ሚሊዮን ዘመነ ፍዳን ሽረው አርነት የሚያወጡ፡፡ እንዲህ ባለው የድባቴ ጊዜ ውስጥ ድንገት ተከስተው ወደ ገነት የሚወስዱኝ አንዳንድ ድምፆች አሉ..የሄመንን አይነት ድምፅ፡፡ ነፍሴ ሳቀች፡፡ በሕይወት ውስጥ ነፍስ የምትስቅበት ቅጽበት አለ እላለሁ..ለእኔ ያ ቅጽበት የሄመን ጥሪ ነው፡፡ ለእኔ ያ ቅጽበት ቆንጆ ሴት በርህን ቆርቁራ ካለህበት ስትመጣ ነው፡፡ ዓለም ከነግሳንግሷ ከፊቴ ላይ ገለል ያለችልኝ ሄመን ስትጠራኝ ነው፡፡

ተነስቼ ወደነሄመን ቤት ሄድኩ፡፡ ሁሌ እንዲህ እንደአሁኑ ቤት ብቻዋን ስትሆን ትጠራኛለች፡፡ እንደ እኔ አራት ሰዓት ይደብራት ይሆን አላውቅም ብዙ ቀን ደብቶኝ በተኛሁበት የአራት ሰዓት ማግስት ላይ ጠርታኝ ቤት ሄጄ አውቃለሁ፡፡ እነሄመን ቤት ከተከራየሁ ስምንተኛ ወሬን ይዣለሁ፡፡ በወር አንድ ጊዜ የሚመጣ ፊታወቅ የሚባል ጓደኛ ቢኖረኝም አብሮኝ እንዳለ አልቆጥረውም፡፡ እሷም ይሄን ብቸኝነቴን ስለምታውቅ ነው መሰለኝ ቤተሰቦቿ ወጣ ሲሉ መጥህ ተጫወት ብቻዬን ነኝ ትለኛለች፡፡

ቤት ስገባ ለስለስ ያለ ሙዚቃ ተቀበለኝ..ዛሬም ሚኪያ እየዘፈነች ነው፡፡ ሁሌ እዛ ቤት ጠርታኝ ስሄድ በሚኪያ በላይነህ ሙዚቃ ነው የምትቀበለኝ።

እዛ ቤት የሚኪያ በላይነህ መብዛት አልገባህ እንዳለኝ ወደ ሳሎን አቀናሁ፡፡ ሄመን ከሙዚቃው ጋር አብራ እየሞዘቀች ቅድም በተላተምኩበት ፒጃማዋ አገኘኋት።

‹ምነው ብቻሽን..እነማዘር የት ሄደው ነው? አልኳት ድምፄን አጥፍቼ ከምገባ ብዬ፡፡

‹ማዘር ክፍለ ሀገር ሄዳለች...

‹እና ብቻሽን ነሻ!..

‹አዎ ሰሞኑን ብቻዬን ነኝ...› አለችኝ በሚያሳዝን ድምፅ፡፡ ድምፅዋ ውስጥ ከብቸኝነት የገዘፈ ሌላ ብቸኝነትን አደመጥኩ፡፡ እኔ ሆኜ እንጂ ፊታወቅ ቢሆን ከዚህ ንግግሯ ውስጥ ብዙ እውነቶችን መዞ ያወጣ ነበር። ብዙ ጊዜ ነገር አይገባህም ይለኛል፡፡ እሱ ብቻ አይደለም እስከዛሬ የተዋወኳቸው ሴቶች ነገር አይገባህም ሲሉኝ አድምጫለሁ፡፡ የሄመን ‹ሰሞኑን ብቻዬን ነኝ› ማለቷ ከወሬ ባለፈ ምን ማለት እንደሆነ ሳይገባኝ ዝም አልኩ። ወር ሙሉ ከአጠገቤ ሲርቅ ያልናፈቀኝ ጓደኛዬ በዓይኔ ላይ አንጃበበ፡፡

‹አባዬም እንደምታውቀው በሥራ ምክንያት አምሽቶ ነው የሚገባው..› ሳልጠይቃት ነገረችኝ። ይሄን ብላ ትታኝ ወደሚቀጥለው ክፍል አመራች። ምሳ እየሠራች እንደሆነ ከሚሰነፍጠኝ የወጥ ሽታ ተረዳሁ። ማዕድ ቤቱ ከሳሎኑ ፊት ለፊት ስለሆነ እንቅስቃሴዋ ሁሉ ይታየኛል፡፡ እኔ ሳሎን ሶፋ ላይ ሆኜ እሷ ማዕድ ቤት ሆና እስኪበቃኝ ቀላወጥኳት፡፡

ቤት ጠርታኝ የሆነ የምወደውን ነገር ሳታደርግልኝ ቀርታ አታውቅም፡፡ ሁሌም አዲስ ነገሬ ናት፡፡ ማዕድ ቤት በስስ ፒጃማዋ ውስጥ የማይታየኝ ነገር የለም። እንደ ጣዝማ ማር የጠየመ ገላዋ የጠለለ የምንጭ ውሀ ይመስል ነበር፡፡ ቀይ ፓንት፣ ጥቁር ጡት ማስያዣ ደረቷንና ወገቧን ዞረው ሳይ ኃጢየት ተሰማኝ፡፡ እዛ ቤት ስገባ የማያቸው የሁልጊዜም ትዕይንቶቼ ነበሩ፡፡ ብዙ ጊዜ አትገባኝም..የማልረዳት ሴት ናት፡፡ ለምንና እንዴት እንደምታስበኝ ሳላውቅ በምትሆነው መሆን እጨነቃለሁ፡፡ ቆይ አንድ ሴት ለአንድ ወንድ እህት ብቻ መሆን አትችልም? እኛ ወንዶች ሴት ልጅ ለፍቅር ብቻ ነው የቀረበችን ብለን እንድናስብ የሚያደርግ የተሳሳተ ሶፍት ዌር የጫነብን ማነው?

በእጇ ምሳ ይዛ ወደሳሎን ተመለሰች፡፡ የዛሬ አዲስ ነገር አብሬአት ምሳ መብላት ነው፡፡ ከእሷ ጋር ምሳ መብላት ምን እንደሚመስል ዛሬ ላየው ነው፡፡ እስከዛሬ ቤታቸው ሄጄ ብቻዬን ነበር ስበላ የነበርኩት፡፡ ከእሷ ጋር መብላትን በእለተ ሐሙስ ከጌታ ጋር በአንድ ማዕድ ከመቀመጥ ጋር አገናኘሁት፡፡ ሳላውቀው ሄመንን እንደ እህት አምኖ መቀበል እየከበደኝ መጣ፡፡ አውቃም ይሁን ሳታውቅ የምታደርገው ነገር ወደማላውቅ ደስታ እየወሰደኝ ነው፡፡

እጄን አስታጥባኝ የመጀመሪያውን ጉርሻ ወደ እኔ ስትሰነዝር የሆንኩትን አረሳውም፡፡ ጉርሻዋ ብርቅ ሆኖብኝ ለረጅም ጊዜ አላመጥኩት፡፡ ያን ጉርሻ ወደ ሆዴ ሳልሰድ ቀን ሙሉ እያላመጥኩት ብውል በወደድኩ ነበር፡፡ ከዛ በኋላ ያልቆጠርኳቸውን ብዙ ጉርሻዎች አጎረሰችኝ፡፡ ሳላጎርሳት ዝም ብዬ መብላት ጀመርኩ፡፡ ባልተቀየመ ልብ ማጉረሷን ተያያዘችው፡፡

እፎይ አልኩ..

ሕይወት እፎይ ማያ ሲኖራት ምን እንደምትመስል ያን ቀን አወኩ፡፡ ፍቅር የሕይወት ሱስ ነው..ሳላውቀው በምታደርግልኝ ነገር ሄመንን ወደድኳት፡፡ ነፍሷ እፎይ ማያዬ ሆኖ አረፈ...

# ዓለም አቀፍ

## ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ በአሜሪካ የመጀመሪያውን ይፋዊ የሥራ ጉብኝታቸውን ሊያደርጉ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዓረብ ኢምሬትስ ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህንያን በአሜሪካ የመጀመሪያቸው የሆነውን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ሊያደጉር ነው።

ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ በአሜሪካ የሚያደርጉትን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት የፊታችን ሰኞ መስከረም 12 እንደሚጀምሩም ከዓረብ ኢምሬትስ የዜና አገልግሎት ዋም ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህንያን የዓረብ ኢምሬትስ ፕሬዚዳንት ሆነው ሥልጣን ከያዙ በኋላ በአሜሪካ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ሲያደርጉ ይህ የመጀመሪያቸው እንደሆነም ተነግሯል።



ፕሬዚዳንቱ በአሜሪካ ነጩ ቤተ መንግሥት ዋይት ኃውስ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ይፋዊ አቀባበል እንደሚደረግላቸውም ተነግሯል።

ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ በአሜሪካ ቆይታቸውም ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ጋር እንዲሁም ከሌሎች ባለሥልጣናት ጋር ውይይት እንደሚያደርጉም ይጠበቃል።

ከዋነኛ የውይይት አጀንዳዎቻቸው ውስጥም ከ50 ዓመታት በላይ ያስቆጠረውን የአሜሪካ እና የዓረብ ኢምሬትስ ስትራቴጂካዊ አጋርነትን የበለጠ ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ እንደሚያተኩር ተነግሯል።

በተለይም በኢኮኖሚ፣ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በቴክኖሎጂ፣ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ እና የህዋ ምርምር እንዲሁም በአየር ንብረት ለውጥ እና በታዳሽ ኃይል ዙሪያ እንደሚመክሩ ይጠበቃል።

ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ እና ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ጋር በዓለም አቀፋዊ እና በቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ እንደሚወያዩም የሚጠበቅ ሲሆን፤ የጋዛው ጦርነት እና የሱዳን ጦርነትን በውይይታቸው ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል ናቸው።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከሁለት ዓመት በፊት በመካከለኛው ምስራቅ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ከዓረብ ኢምሬትስ ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ ጋር ተገናኝተው መምከራቸው ይታወሳል።

ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከፕሬዚዳንት ሼህ መሐመድ ቢን ዛይድ ጋር ባደረጉት ውይይትም ከዓረብ ኢምሬትስ ጋር ያለውን ግንኙነት በሚጠናከርበት ዙሪያ መምከራቸው ይታወሳል።

## እስራኤል በኔታንያሁ ላይ ያነጣጥር የነበረ የግድያ ሴራን አከሸፍኩ አለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እሥራኤል በጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ላይ ሊቃጣ የነበረ የግድያ ሙከራን ማክሸፏን አስታወቀች።

የሀገሪቱ ፖሊስና የደኅንነት መሥሪያ ቤት (ሺን ቤት) በጋራ ባወጡት መግለጫ፥ በኢራን በሚደገፈው የግድያ ሴራ ሲሳተፍ ነበር የተባለ እሥራኤላዊ በቁጥጥር ስር መዋሉን ገልጸዋል።

ተጠርጣሪው ኔታንያሁ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ ዮቭ ጋላንት እና የሀገር ውስጥ የደኅንነት ተቋሙ ኃላፊ የሚገደሉበትን መንገድ በተመለከተ በተደረጉ ውይይቶች ተሳትፏል ይላል መግለጫው።

በቁጥጥር ስር የዋለውን ተጠርጣሪ ስም መግለጫው ባይጠቅስም የእሥራኤል መገናኛ ብዙኃን የ73 አመቱ የአሽኬሎን ከተማ ነዋሪ ሞቲ ማማን መሆኑን ዘግበዋል።

ለቢዝነስ ጉዳይ ለመምከር በቱርክ አድርጎ ወደ ኢራን እንደገባ ከቴህራን መውጣት እንደማይችል የተነገረው ተጠርጣሪው ከኢራን የደኅንነት ባለሥልጣናት ጋር እንዲገናኝ ተደርጎ ተልዕኮዎች እንደተሰጡት ነው ሺን ቤት የገለጸው።

ለቴህራን ገንዘብና መሣሪያዎችን ማዘዋወር፣ በእሥራኤል ሰዎች በብዛት የሚገኙባቸውን አካባቢዎች ፎቶግራፍ አንስቶ መላክና ሌሎች ተልዕኮዎች ተሰጥቶት ወደ እሥራኤል ቢገባም የተባለውን ሳያደርግ ዳግም ወደ ኢራን መመለሱንም ጠቅሷል።

በነሐሴ ወር ወደ ኢራን ሲመለስ የሽብር ጥቃት እንዲፈጽም አልያም የእሥራኤል ባለሥልጣናትን እንዲገድል ጥያቄ ቀርቦለት 1 ሚሊዮን ዶላር እንዲከፈለው ጠይቆ የቴህራን ባለሥልጣናት ጥያቄውን ሳይቀበሉት መቅረቱንም ነው መግለጫው ያብራራው። በግድያ ሴራ ስብሰባዎቹ በመሳተፉ ግን 5 ሺህ 570 ዶላር እንደተከፈለውም በመጥቀስ።

እሥራኤል፥ በኢራን የሀገሪቱን ዜጎች ጭምር በመመልመል የስለላ ሥራ የማከናወን የረጅም ጊዜ ልምድ አላት። በሐምሌ ወር የሃማስ መሪ ኢስማኤል ሃኒየህ በቴህራን መግደሏም የዚህ ማሳያ ተደርጎ ይነሳል።



ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# የመስከረም ድምቀት- የጉራጌ ባሕላዊ እሴቶች



**ዳግም ከበደ**

መስከረም ሲጠባ ኢትዮጵያውያን በልዩ መንገድ ገጽታቸው ይፈካል፤ አለባበሳቸው ይደምቃል። የነሐሴ ጨለማ የጳጉሜን ካፊያ ለበጋው ወራት ተራቸውን ለመልቀቅ ዳር ዳር ይላሉ። የክረምቱ ማብቂያ መስከረም የኢትዮጵያውያንን ገፅታ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያንንም መልከዓ ምድር ያፈካዋል። ሜዳው ሸንተረሩ፣ ደጋው ወይና ደጋው አረንጓዴ ይለብሳል፤ ሰብል ደረስኩ ደረስኩ ይላል። ይህ ወቅት የመላው ኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመት የሚገባበት፣ ያለ ልዩነት ሁሉም በአንድነት ለመጪው ዓመት የሚዘጋጅበትም ነው።

ሜዳ ተራራው በአደይ አበባ ይደምቃል፤ ቢጫ ይሆናል፡፡ ቢጫ ቀለም ተስፋ እንደሆነው ሁሉ አደዩም የሀገሪቱን መልከዓ ምድር ቢጫ ቀለም በማልበስ ይህን ተስፋ ያስተጋባል፡፡

በመስከረም ወቅት ልክ ሜዳው ሸንተረሩ በአንድ አደይ አበባ እንደሚደምቀው ሁሉ ኢትዮጵያውያንም ይዋባሉ። ዘመድ፤ ወዳጅ፣ ቤተሰብ ይጠያየቃል። በየአቅጣጫው እንቅስቃሴዎች ይበዛሉ፡፡

ተማሪዎች እውቀትን ለመገበየት የሚናፍቁበት ወር ነው፤ ወርሀ መስከረም። በመስከረም ሰው ብቻ ሳይሆን የቤት እንስሳቱ ይጠግባሉ፤ ከብቶች ለግጦሽ በተዘጋጀ ሜዳ ላይ ይቦርቃሉ። ምን አለፋችሁ መስከረም ለመላው ኢትዮጵያውያን የአዲስ ተስፋ፣ የአዲስ እሳቤ፤ የአዲስ ዓመት መግቢያ ወር ነው።

በወርሀ መስከረም በሁሉም ዋልታ ለኢትዮጵያውያን በዓል ነው። ለዛሬ ግን እኛ ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሉ ጉራጌ ብሔረሰብ ዞኖች ለመሄድ ወደናል። የጉራጌ ብሔረሰብ ልክ እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች በቱባ እውቀት፣ ባሕልና እሴቶች ባለጸጋ ነው። በአንድ ጊዜ ‹‹እንዲህ ናቸው›› ተብለው ተነግረው የማያልቁ ተወዳጅና አስደናቂ እውቀቶች ባለቤት ነው።

የጉራጌ ብሔረሰብ የሚኖርባቸው የአሁኑ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሁለቱ የጉራጌ ዞኖች/ ቀደም ሲል ዞኑ አንድ ነበር/ በመስከረም ከሚደምቁ፣ በፍቅርና በደስታ ከሚያብቡ የኢትዮጵያ ክፍሎች ውስጥ ቀዳሚዎቹ ናቸው። ‹‹መስከረም ሲጠባ በመስቀል በዓል በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ ጭር ይላል›› እስከ መባል መድረሱም ይታወቃል። በከተማዋ የሚኖሩ የብሔረሰቡ ተወላጆች የመስቀል በዓልን ለማክበር፣ ቤተሰቦቻቸውን ለመጠየቅ ፣ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ስለሚተሙ ነው ይህ መባሉ።

በተለይ መስከረም 17 ቀን ለሚከበረው የመስቀል በዓል የጉራጌ ብሔረሰብ በሚኖርባቸው የክልሉ ዞኖች ልዩ የበዓል ዝግጅት ይደረጋል። ማህበረሰቡ መስቀልን በዋዜማው እንዲሁም በእለቱ ብቻ አይደለም የሚያከብረው፡፡ ሰሞኑን ሁሉ በበዓላቱ ይደምቃሉ፡፡

በዓሉን ለማክበር ዓመቱን ሙሉ ነው ዝግጅት ይደረጋል። ይህም የማህበረሰቡን ብልሀት እንዲሁም ጥብቅ እሴት ያመለክታል። የጉራጌ ብሔረሰብ ለበዓል የሚያደርጋቸው ዝግጅቶች በባሕላዊ ሥነ ሥርዓቶች የታጀቡ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር የእለት ተእለት ማህበራዊ ሕይወቱን የሚያከናውንባቸው ሀገር በቀል እውቀቶችና እሴቶችም ሞልተውታል። ለዛሬ ከእነዚህ እሴቶች መካከል ጥቂቱን ይዘን ቀርበናል፡፡

## ያጋ ቃዋ - የጉራጌ ማህበረሰብ የቡና ሥነ ሥርዓት

የጉራጌ ማህበረሰብ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ከሚያቀራርቡላቸው ወይም ከሚያጠነክሩላቸው መልካም እሴቶች መካከል ‹‹ያጋ ቃዋ›› የሚሉት የቡና አጠጣጥ ሥነ ሥርዓት አንዱ ስለመሆኑ ከጉራጌ ዞን ባሕልና ቱሪዝም መምሪያ ሕዝብ ግንኙነት ክፍል ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህ የቡና አፈላል ሥርዓት በመስከረም ወር በተለይ በመስቀል በዓል ወቅት ደምቆ ይታያል፤ በልዩ ሁኔታ ይካሄዳል።

መረጃው እንዳመለከተው፤ የጉራጌ ማህበረሰብ ካለበት ቀዬ አቅራቢያ ከሚገኙ ጎረቤቶቹ ከሶስት እስከ ስድስት አባላት በመሆን ቃዋ (ቡና) ይጠጣል። የቡና አፈላል ሂደቱ የሚከናወነው ተራ በተራ ነው፡፡ ዛሬ በአንዱ አባ ወራ ቤት ከተፈላ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተራውን ጠብቆ በሌላኛው አባወራ ቤት ይፈላል፡፡ ይህ ዓይነቱ የቡና አጠጣጥ ሥነ ሥርዓት ያጋ ቃዋ በመባል ይታወቃል፡፡ ጠዋት ላይ የሚካሄደው የቡና አጠጣጥ ሥነ ሥርዓት ያጋ ቃዋ ሲባል መሸት ሲል ተጠራርተው የሚጠጡት ቡና ደግም ዮጌር ቃዋ (ሸንጎ ቡና) ተብሎ እንደሚጠራ ያስረዳል፡፡

‹‹ያጋ ቃዋ›› እጅግ በጣም ተወዳጅ የሆነ የቡና አጠጣጥ ሥነ ሥርዓት ነው። ሰዎችን እርስ በርስ የሚገናኝና የሚያዋድድ፣ የሚያፋቅርና የሚያስተሳስብ ስለሆነ ጉራጌዎች ለያጋ ቃዋ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጡት መረጃው ይጠቁማል፡፡ ባለተራዋ እማወራ ሌሊት ወፎች ከመንጫጫታቸው በፊት አስቀድማ በመነሳት ‹‹ቦሄ ያትየደርሄ ጌታ ቦሄ አወሬ›› (ሰላም ያሳደርከኝ አምላክ ሰላም አውለኝ) በማለት ለአምላኳ ምስጋና ካቀረበች በኋላ ተጣጥባ ቡና የማፍላት ዝግጅቷን እንደምትጀምር አመልክቶ፣ ሥርዓቱ በደማቅ ማህበራዊ ትስስር እንደሚቀጥል ጠቁሟል።

## ጀፎር- የብሔረሰቡ የመንገድ ምህንድስና ጥበብ

መረጃው እንዳብራራው፤ ብሔረሰቡ የራሱ የሆነ የመንገድ ምህንድስና ጥበብም አለው፡፡ ከጉራጌ ማህበረሰብ እሴቶችና ሀገር በቀል እውቀቶች ውስጥ አንዱ የሆነው ይህ የምህንድስና ጥበብ ‹‹ጀፎር›› በመባል ይታወቃል፡፡ በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ስለዚህ ሀገር በቀል እውቀት አንስተው በኢትዮጵያ የሚገነቡ መንገዶች ከጉራጌ ማህበረሰብ ሀገር በቀል እውቀት ብዙ ሊጋሩ እንደሚገባቸው መናገራቸው ይታወሳል።

የመንደር አመሰራረቱና ‹‹ጀፎር›› የተሰኘው የባሕላዊ የአውራ መንገድ ቅየሳ ወይም የምህንድስና ጥበብ አንዱ የብሔረሰቡ ሀገር በቀል እውቀት መሆኑን መረጃው ይጠቁማል። "ጀፎር" ማለት የጉራጌኛ ቃል ሲሆን አውራ መንገድ ማለት ነው፡፡ ታዲያ ይህ የ"ጀፎር" ፍልስፍና በጉራጌዎች መንደር የተጀመረው ገና ሀገራችን ባለ አራት እግር የሞተር ተሽከርካሪዎች ሳይገቡና የመኪና ስሙ እንኳን በማይታወቅበት ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት እንደነበረ የጉራጌ አባቶች እንደሚያስረዱ መምሪያው ይጠቁማል።

የጀፎር የጎኑ ስፋት ከ60-100 ሜትር እንደሚወስድ የሚገለጽ ሲሆን፣ ርዝመቱ ግን አውራ መንገድ (ጀፎር) በሚያቋርጥባቸው አቅጣጫዎች ወንዝ፣ ደንና ትልልቅ ሸለቆዎች እስካላጋጠመው ድረስ ቅያሱ ይቀጥላል፡፡ የመንገዱ ስፋት የሚለካውም በባሕሉ መሠረት በተመረጡ አባቶች ወይም የመሬት ልኬት ዳኞች መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ጀፎር በሁለት መንደሮች ትይዩ በመካከላቸው አቋርጦ የሚያልፍና አረንጓዴ ሣር የለበሰ ውብና ጽዱ ባሕላዊ አውራ መንገድ ነው።

በመስከረም ወቅት ልዩ የበዓል ድባብ በዚህ አውራ ጎዳና (ጀፎር) ላይ ይስተዋላል። ማህበረሰቡ በእነዚህ አረንጓዴና ፅዱ ጎዳናዎች ላይ በባሕላዊ አልባሳት ደምቀው ይታያሉ። ሕፃናት ይቦርቃሉ፤ የቤት እንስሳት ለምለም ሣር እየተመገቡ በዓሉ በድምቀት ያልፋል።

## ጡር (ባሕላዊ ሽምግልና ሥርዓት)

የጉራጌ ማህበረሰብ በበዓላት ወቅት ብቻ አይደለም አብሮ የሚበላው፤ የሚጠጣው። የደስታ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይም ይተባበራል። ከዚህ ውስጥ በነዋሪዎች መካከል በሚነሳ አለመግባባት፣ ዘመድ ከዘመድ፣ ጎረቤት ከጎረቤት ቢቀያየም እና ፀብ ቢፈጠር አለመግባባቱን የሚፈታበት የራሱ ባሕላዊ ሥርዓት አለው። ይህ ሥርዓት ‹‹ጡር›› ይባላል።

ጉራጌ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ባሕላዊ ሸንጎ ያስቀመጣቸውን ማህበራዊ ሥርዓቶችና ድንጋጌዎችን ጠብቆ ከሁሉም ጋር በሰላም፣ በመቻቻልና በፍቅር ይኖራል፤ ይህን እንዲያደርግ ካስቻሉት ባሕላዊና መንፈሳዊ እሴቶች አንዱ ጡር መሆኑንም መረጃው ያመለክታል፡፡

በጉራጌ ታሪክ ጡር በሁለት መንገድ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ አንዱ መንገድ ሰዎች በብዙ በደል በብዙ መገፋትና ስቃይ ታግሰው አምላኬ ለትውልዴ ለዛሬ የተሻለ ቀን ያመጣል፣ ስለዚህ በእኔ ላይ የሚፈፀመው ግፍ አንድ ቀን ያቆማል ብለው ተስፋ በማድረግ የሚያገኙት መልካም ነገር ነው፡፡

በዚህ ሁሉ ትዕግስት ተበዳዩ ለበዳዩ ሁልጊዜ በአምላኩ ፊት ቆሞ ‹‹ኤበርየ ጡር የህርብኸ፣ ጡራኸ ይያ ሸመነ የግባ›› በአማርኛው ‹‹እገሌ ጡር ይሁንብህ፤ ጡርህ እኔ ቤት ይግባ›› በማለት ከአንደበቱ ቃል አውጥቶ ይናገራል፡፡

እግዚአብሔር አምላክም የምስኪኖች ወዳጅ ነው፤ የችግረኞችን ጩኸት ከመስማት ዝም ያለበት ጊዜ የለም ሲሉ አባቶች እንደሚናገሩ መረጃው ይገልጻል፡፡ በዚህ ሁኔታ በእግዚአብሔር ጊዜ የበዳዩ ቤት ጡር ወደ ተበዳዩ ቤት እንደሚዞር የባሕላዊ ሸንጎ አካላት ይገልጻሉ፡፡ ይህንን እውነታ በምሳሌ ሲያስረዱ አንዳንድ ጊዜ አንድ አያት ከወለዳቸው ቤተሰቦች መሀል እንኳ ባላቸው ሀብትና የልጅ ብዛት ትልቅ ልዩነት ይከሰታል፡፡

የቀደሙት የፖለቲካ ሥርዓቶች ሴቶችን ከንብረትም ሆነ ከመሬት ባለቤትነት ያገሉ የነበረና ባሕሉም በራሱ ለወንዶች ያደላ የነበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዙ ወንድ ልጆች የወለደ አባት ወንድ ሳይወልድ የቀረን የወንድሞቹን ሴት ልጆች በመግፋት መሬቱን ለራሱ በመከለል በመጨረሻም ለራሱ ልጆች ያከፋፍላል እንበል፡፡ ይህ ዓይነቱ መሬት በባሕሉ የፈነጠበያር አፈር ይባላል፡፡

ሴቶች ልጆቹም በኃይል መሬታቸውን ሲቀሙ ማስጣል ስለማይችሉ መስማት ለሚችለው አምላክ አባታችንና አጎታችን ከአንድ እናትና አባት የተገኙ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ፤ ዛሬ ግን አባታችን ወንድ ባለመውለዱ የተነሳ እኛን ሴቶች ልጆቹን ገፍቶ መሬታችንን ወሰደ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ዓይን አለህና ይህን በደሉን እይበት፤ ጡር ይሁንበት፤ በእኛ ላይ እንደሆነብን በተራ በእርሱም ቤት እንዲሁ ይሁንበት፤ እኛም ዛሬ በተገፋንበትና በተበደልንበት ለልጆቻችንና ለዘራችን ጡር ይግባልን ይላሉ፡፡ ማንም የዘራውን ማጨዱ አይቀርምና በዳይ አጎት የእጁን እንደሚያገኝ ሽማግሌዎች ያመለክታሉ፡፡

ሁለተኛው ጡር የሚወጣበት ሁኔታ ደግሞ አንድ ሰው አባት፣ አያት፣ ቅድመ አያት ወዘተ ያቆዩለትን ጡር እርሱ ስልጣኑን ወይም ሀብቱን ያለ አግባብ ተጠቅሞ በሰዎች ላይ ግፍ በመፈፀምና የሰዎችን መብት በመግፈፍ በሚፈፅመው በደል የተነሳ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ቤቱ የቆየውን ጡር ገፍቶ ሲያስወጣው ሲሆን፣ ይህም በጉራግኛ ‹‹ጡር ተቤተህዎ አነሞ ወጣም›› (ጡር ከቤታቸው ጮሆ ወጣ) ይባላል ሲል መረጃው ያብራራል፡፡

ጉራጌ አንዱ ተበዳይ ጊዜ በሰጠው ሰው ወይም ጉልበተኛ ሲበደል ሲያይ ለተበዳዩ ‹‹ጡር የህርኸ›› ‹‹ጡር ይግባልህ›› እንደሚለው መረጃው አመልክቶ፣ ለበዳዩ ደግሞ ‹‹ጡር የህርብኸ›› ማለትም፡- እግዚአብሔር የሰጠህን መልካም ነገርህና ጸጋህን ካንተ ላይ አንስቶ ይውሰድ እንደማለት ነው ሲል ያብራራል፡፡ ይህ ደግሞ ጉራጌን በሕይወት ጉዞው ነገሩ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠና ሊሰወር እንደማይችል በመረዳት በፍርሃት፣ በቅንነትና በትዕግስት እንዲመላለስ አስችሎታል፡፡

ስለሆነም ባሕሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ በየትኛውም ማዕዘን የሚኖር ጉራጌ ነፍስ ማጥፋትን፣ በሀሰት መመስከርን፣ ቤት ማቃጠልን፣ ግፍ መሥራትን፣ ድንበር ማለፍን፣ ክህደትን፣ የሰው ሀብት መንጠቅን እና ሌሎች ያልተገቡ ነገሮችን በእጅጉ ይጠየፋል፡፡ የብሔረሰቡ ባሕል እሴት የሆነው ‹‹ጡር›› ሰዎች ከክፉ እንዲርቁና መልካሙን እንዲያደርጉ ያደርጋቸዋል፡፡

## እንደ መውጫ

የዝግጅት ክፍላችን ለዛሬው ሀገርኛ ዓምድ ከላይ ባነሳናቸው የጉራጌ ባሕላዊ እሴቶች ላይ ያተኮረ እንጂ ማህበረሰቡ በመስከረም ወቅት በሚያከብረው ተወዳጅና ተናፋቂ በሆነው የመስቀል በዓል ወቅት ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ባሕላዊ ክንውኖችም አሉት። ከእነዚህ መካከል የአመጋገብ ሥርዓት አንዱ ሲሆን፤ በተለይ የእርድ ሥነ ሥርዓቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት ይታወቃል። ከእንሰት፣ ከሥጋ፣ ከጎመን እንዲሁም ከተለያዩ ተዋጽኦዎች የሚዘጋጀው የክትፎ፣ ቆጮ አይቤ እና ልዩ ልዩ ምግቦች የመስከረም ድምቀቶች የኢትዮጵያውያን ተወዳጅ ምግቦች መሆናቸው ተመስክሮላቸዋል።

**ሰላም!!**

# ኢትዮጵያ እና የጤና ዲፕሎማሲ

**ከመላኩ ሙሉዓለም ቀ.**
**በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የሥልጠና ዳይሬክተር ጄኔራል**
melakumulu@yahoo.com

የሰው ልጅ በዚህ ምድር መኖር ከጀመረ ጀምሮ እስካሁን አንድ መቶ ስምንት ቢሊየን ሰዎች የኖሩበት እንደሆነ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በእርጅና፣ በተፈጥሮ አደጋ፣ በጦርነት፣ በረሀብ፣ በተለያዩ የበሽታ ዓይነቶችና ወዘተ ምክንያቶች አንድ መቶ ቢሊየን ሰዎች ሞተዋል፤ ቀሪው ስምንት ቢሊየን ሕዝብ አሁን በሕይወት ይገኛል፡፡ ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ ደግሞ ጥቂት ታሪክ ተናጋሪዎች ብቻ ሲቀሩ አሁን በሕይወት ያሉት ሰዎች አልፈው በሌሎች አዲስ ትውልዶች ይተካሉ፡፡ ይህ የተፈጥሮ ግዴታና እውነታ ነው፡፡

ቶማስ ሮበርት ማልተስ የሚባል ሰው (እ.ኤ.አ 1766-1834 የኖረ) የዓለምን ሕዝብ በተመለከተ በፃፈው ጥናትና ንድፈ ሃሳብ (ቲዩሪ) የዓለም ሕዝብ ከሚመገበው የምግብና ሌሎች ሪሶርስ አንፃር ብዛቱ ካልተመጣጠነ በዓለም ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጠራል ይላል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች መኖርና የሕዝብ ቁጥር መቀነሱ አስፈላጊ ነው ይላል፡፡ ይህ ሃሳብ ደጋፊም ተቃዋሚም ያለው ነው፡፡

ለመንደርደሪያ ያክል ይህንን ካነሳን የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ ሲኖር በጤና እንዲኖር ሀገራት የራሳቸው ፖሊሲና ሕግ ቀርፀው ይሰራሉ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም የጤና ድርጅቶች ተቋቁመው በሥራ ላይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ሀገራችንም ኢትዮጵያ የዜጎችን ጤንነት በተመለከተ በሕገ መንግሥት አንቀጽ 90 ላይ እንደደነገገችው የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የጤና አገልግሎት እንዲኖረው ይደረጋል ይላል፡፡

በዚህ መሠረት በሀገራችን ላይ ያለው የጤና ሽፋን እየተስፋፋ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም። ብዙ መሥራትን ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ሰፋ ያለ ሥራ ከሌሎች ሀገሮችና ዓለም አቀፍ የጤና ተቋማት ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት በዲፕሎማሲ ማጠናከር ተገቢ ነው፡፡ ይህም ተግባር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የጤና ሚኒስቴር የጋራ ሥራ ይሆናል ማለት ነው፡፡

የዚህም ጽሑፍ ዋና አላማ የጤና ዲፕሎማሲ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን ሀገራችን ከአላት ሀብት በተጨማሪ የሌሎችን ድጋፍና ትኩረት በመሳብ ከጤና ጋር ያሉብንን ችግሮች ለመቅረፍ ሲሆን፤ እንደአስፈላጊነቱም ኢትዮጵያ ያላትን ውስን ሀብት ለሌሎች ሀገሮች የምታካፍልበትንም ለመጠቆም ነው፡፡ ከርዕሱ ለመረዳት እንደሚቻለው የጤና ዲፕሎማሲ የሚለው ሃሳብ የጤና ሥራ እና የዲፕሎማሲ ሥራ ተናበውና ተቀናጅተው መሥራትን ያመለክታል፡፡

የሀገራችንን የጤና ዲፕሎማሲ ታሪካችንን በተመለ ከተ የውጭ ሀገር ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ መድኃኒቶችን እንዲያመጡና የህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረግ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የቀድሞ ነገሥታትም የውጭ ሀገር የህክምና ባለሙያዎችን በማስመጣት የግል ሐኪሞች በማድረግ ይጠቀሙ ነበር፡፡ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ የባሕል መድኃኒቶችን ከበሽታ ለመፈውስ ይጠቀም ነበር፡፡

ጣልያን በወረረችን ጊዜ በርካታ ሀገሮች የገንዘብ፣ የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሰረተው ሆስፒታል የዳግማዊ አጼ ምኒልክ መታሰቢያ ሆስፒታል ሲሆን በ1901 ዓ.ም ነበር የተመሰረተው፡፡ ይህም ሆስፒታል መመስረት አሁን ለደረሰንበት የህክምና ሥራ ጥሩ መሰረት ሆኗል፡፡

ከዲፕሎማሲ አንፃር በሀገራችን የተመሰረቱ ሆስፒታሎችን ስንመለከት ደግሞ የጋንዲ ሆስፒታል እ.አ.አ በ1958 ዓ.ም በህንድ የተመሰረተ፤ የዓድዋ ጦርነት ጀግና በሆኑት የደጃዝማች ባልቻ ስም እ.ኤ.አ 1947 በሩስያ ቀይ መስቀል የተመሰረተ ሆስፒታል፤ እ.ኤ.አ 2008 የቤጂንግ-ቻይና አሎምፒክ ሁለት ወርቅ በአመጣችው የጥሩነሽ ዲባባ ስም የተሰየመው ሆስፒታል በቻይና ተገንብቶ ወደ ሥራ ገብቷል።

በኮሪያ ጦርነት ያደረግነውን ድጋፍ ታሳቢ ያደረገ በቅርብ ዓመታት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ የተሰራው የኮሪያ ሆስፒታል እንዲሁም በርካታ የጤና ተቋማትና በውጭ ሀገራት ድጋፍ ተቋቁመው በሥራ ላይ እናገኛቸዋለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ የዓለም የጤና ድርጅት (WHO)እና የበርካታ የጤና ተቋማት አባል በመሆኗ የጤና ድጋፎችን እያገኘች ነው፡፡ ይህ ተግባር በሀገራችን ያለውን የሀብት ውስንነት በመቅረፍ የጤና ሽፋን አሁን ከአለው በተሻለ ደረጃ ለማድረስ ያግዛል፡፡

ዲፕሎማሲ ማለት ሰጥቶ መቀበል መርህን የሚከተል እንደመሆኑ ከጤና ዲፕሎማሲ ሥራ ኢትዮጵያ የምትቀበለውን ድጋፍ ብቻ ትኩረት ማድረግ ሳይሆን ለሌሎችም መስጠት የምትችለውን የሚመለከት ነው። ለአብነት ያክል የኢቦላ ወረርሽኝ በምዕራብ አፍሪካ ሲስፋፋ ኢትዮጵያ ሁለት መቶ(200) የሚሆኑ የህክምና ባለሙያዎችን እና የገንዘብ ድጋፍ በመላክ የጤና አጋርነቷን አሳይታለች፡፡

በተመሳሳይም የኮቪድ ወረርሺኝ ዓለምን ባስጨነቀበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት የህክምና እና የበሽታ መከላከያ ቁሳቁሶችን በመውሰድ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች፡፡ እ.ኤ.አ. በ2018 ኢትዮጵያ ሰላሳ አምስት ዶክተሮችን ወደ ኤርትራ በመላክ የበጎ ፈቃደኛ አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጋለች፡፡

የጎረቤት ሀገራትን ከመደገፍ አንጻርም ኢትዮጵያ የተለያዩ ሀገራት የህክምና ዶክተሮች በሀገራችን እንዲማሩ አድርጋለች፡፡ ለአብነት ያክል አንድ መቶ አርባ አምስት(145) የደቡብ ሱዳን ወጣቶች የህክምና ትምህርት(ዶክትሬት) በሀገራችን እንዲያገኙ ስኮላርሺፕ ሰጥታለች፡፡ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ኔዘርላንድ ለደረሰባት የተፈጥሮ አደጋ ኢትዮጵያ ድጋፍ የሰጠች መሆኑ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

የጤና ዲፕሎማሲ ማከናወን በርካታ ጥቅሞችን የሚያመጣ ሲሆን አቅም በፈቀደ መጠን ለተቸገሩ ስንደርስ የጋር ኃይልን (soft power) ለማስፋት የሚያግዝ ሲሆን፤ አቅማቸው ከፍ ያሉ ሀገራት ጋር በሚኖረን የዲፕሎማሲ ግንኙነት ደግሞ ያሉብንን ክፍተቶች ለመሙላት የሚያግዝ ድጋፍ እናገኝበታለን፡፡ የጤና ዲፕሎማሲ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች ውስጥ በዋናነት የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

### የጤና ጋር የተያያዙ መዋዕለ ነዋይ (ኢንቨስትመንት) ከውጭ ለመሳብ

በሀገራችን የሚገኙ የውጭ ኢንቨስትመንቶችን ስንመለከት በዋናነት ምርት ላይ ያተኮሩ ናቸው (manufacture)፡፡ በጤና ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ የውጭ ባለሀብቶች ግን እጅግ አነስተኛ ናቸው፡፡ ጤና ዙሪያ ኢንቨስት ማድረግ የሚችሉ ባለሀብቶች ወደ ሀገራችን መጥተው እንዲሰሩ ማድረጉ የተሻለ ህክምና ለማግኘት ወደ ውጭ ሀገር እየሄዱ የሚታከሙ ዜጎችን በሀገራቸው እንዲታከሙ ማድረግ የሚያስችልና አዋጭ መሆኑን ለባለሀብቶች ማሳየት ተገቢ ነው፡፡

በጤና ዘርፍ ኢንቨስት የሚያደርጉ የዲያስፖራ አባላት ወይም የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለአብነት ያክል በቻይና ኢንቨስት የተደረገው Silk Road General Hospital መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ሆስፒታል በኢትዮጵያ እንዲመሰረት ለማድረግ የተቻለው ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራ ተሰርቶ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የጤና ሽፋንን ለማስፋት የጤና ዲፕሎማሲ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ይፈልጋል፡፡

### የእውቀት ሽግግር ለማከናወን

በጤና ዲፕሎማሲ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ ከጤና ጋር የተያያዙ ከአደጉ ሀገሮች የሚፈስ እውቀት አንዱ ነው፡፡ ጤናን በተመለከተ አዳዲስ ፈጠራዎች ወደ ሀገራችን እንዲገቡ በማድረግ የህክምና አገልግሎትን ጥራት መጨመር ይቻላል፡፡ የእኛም የጤና ዲፕሎማሲ በሥራ ላይ ለሚገኙ የህክምና ዶክተሮችና ባለሙያዎች የስኮላርሺፕ በማመቻቸት አዳዲስ የህክምና መሣሪያዎች ወደ ሀገራችን እንዲገቡ በማድረግ፣ በጎ ፈቃደኛ ሐኪሞችን (Volunteer) ወደ ሀገራችን መጥተው የተለየ እውቀታቸውን የሚያስተላልፉበትና ወዘተ ሥራዎችን መሥራት ያስችላል፡፡

### ፋይናንስ ለማፈላለግ

በሀገር ደረጃ ያለውን የጤና ፍላጎት ለማሟላት የመንግሥት በጀት ብቻውን ከአንድ መቶ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ለአላት ሀገር በቂ እንዳልሆነ ይታወቃል።በመሆኑም በጤና ዲፕሎማሲ ከተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጋር በመገናኘትና የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት ለሀገራችን የጤና ሥራ የሚያገለግል ፋይናንስ ማግኘት ይቻላል፡፡ በተለይ ከፍለው መታከም የማይችሉ ዜጎችን ለማከም የሚደረገውን ፍላጎትና ተግባር ለማገዝ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ የጤና ሚኒስቴር ከተለያዩ ተቋማት ጋር በአጋርነት እየሰራ እንደሚገኝ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ ያሳያል፡፡ ይህንን ማስፋት የሚቻለውም በጤና ዲፕሎማሲ ነው፡፡

### ጤና የሚጎዱ ምርቶች ከውጭ እንዳይገቡ ለማገድ

ዲፕሎማቶች ከተመደቡበት ሀገር እና ከሌሎች ሀገሮች ወደ ሀገራችን የሚገቡ ምርቶች ጥራት ላይ መረጃዎችን በማሰባሰብ መንግሥትን የሚመክሩበትና አላስፈላጊ ምርቶች ሰርገው ገብተው የጤና ችግር እንዳይፈጥሩ የማድረግ ሥራን ሊያግዙ ይችላሉ፡፡ በተለይ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ያመዘኑ እና ደረጃቸውን ያልጠበቁ መድኃኒቶች ከውጭ እንዳይገቡ ለማድረግ ያስችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት መድኃኒቶች ሁለት ጉዳቶችን ያመጣል፡፡ አንዱና ዋናው ጉዳት የታመሙ ሰዎች መድኃኒቱን ተጠቅመው መዳን አይችሉም፤ የጎንዮሽ ችግርም ሊያመጣባቸው ይችላል። ሁለተኛው ችግር ደግሞ ማዳን የማይችል መድኃኒት ለመግዛትና ለማጓጓዝ የውጭ ምንዛሪ መውጣቱ ነው፡፡ የጤና ዲፕሎማሲ ይህንን የመሰለ ዘርፈ ብዙ ኪሳራ ሊታደግ ይችላል፤፤

### በዓለም ላይ የሚከሰቱ ወረርሽኞች ወደ ሀገር እንዳይገቡ የጥንቃቄ ሥራ ለማከናወን

በተለያዩ ጊዜያት በዓለማችን ላይ ወረርሽኞች ይነሳሉ፡፡ ከአንዱ ሀገር ወደሌላው በመዛመት ሕዝብ ይጨርሳሉ፡፡ የቅርቡን ኮቪድ 19 እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይህን መሰል ወረርሽኝ ሲነሳ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲደረግ ለማድረግና የሚፈጥረውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ያስችላል። በተለያዩ ሀገራት የተመደቡ ዲፕሎማቶች ስለተመደቡበት ሀገር የጤና ሁኔታ ላይ መረጃ ለማግኘት ብዙም አይቸገሩም፡፡ ይህ መረጃ ግን ለሀገራችን የጤና ሥራ በጣም ጠቃሚ ነው። በሽታ እንዳያስተላልፉ እንደአስፈላጊነቱ ወደ ሀገራችን ሰዎች እንዳይገቡ ቪዛ እስከ መከልከልም የሚያደርስ ውሳኔ ሊያስከትል ይችላል፡፡

### ከጤና ጋር የተያያዙ ድርድሮችን ለማከናወን

ሀገራት የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ የሚያከናውኑ ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ የድርድር ክህሎት ወሳኝ ነው፡፡ ይህ ክህሎት በዋናነት በዲፕሎማቶች አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት የድርድር ተግባራትን የማገዝ እና የብሔራዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ሥራ ለማከናወን ያግዛል፡፡ ከድርድር በፊት የሚከናወኑ ቅድመ ዝግጅቶች ላይም ዲፕሎማቶች የተለያዩ ሥራዎችን ሊሰሩ ይችላሉ። በተለይ ድርድሩ በውጭ ሀገር የሚደረግ ከሆነ ዲፕሎማቶች ቅድመ ድርድር ላይ ዝግጅትን ያግዛሉ፡፡ የድርድሩ ውጤት አተገባበር ላይም የጤና ዲፕሎማሲ መሥራት ያስችላል፡፡

### ሀገራችን የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር መከታተል

በዓለማችን ላይ ከጤና ጋር የተያያዙ በርካታ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አሉ፡፡ ኢትዮጵያም የፈረመቻቸው በርካታ ናቸው፡፡ ለአብነት ያክል በ1927 ዓ.ም. ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር አባል ሆናለች። የእነዚህ ስምምነቶች አፈፃፀም ላይ በጤና ሚኒስቴር የሚቀርቡ ሪፖርቶች አቀራረብ ላይ በዲፕሎማሲ ሥራ ማገዝ ያስችላል፡፡ የሚቀርቡ ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትም እንዲደርስ ያግዛል፡፡

### ዲያስፖራ ማህበረሰብን በጤና ዘርፍ ማሳተፍ

በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ የሆነ የእውቀት፣ የማቴሪያል እና የገንዘብ ሀብት ባለቤቶች ሆነው ይገኛሉ። እነዚህ የዲያስፖራ ማህበረሰብ ወደ ሀገራቸው ገብተው በጤና ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ የህክምና መሳሪያ እና መድኃኒት እንዲያበረክቱ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተለይ የህክምና ትምህርትና የሥራ ተሞክሮ ያላቸው የዲያስፖራ አባላት በሀገራችን ያለውን የጤና ክፍተት እንዲሞሉ በማስተባበር በርካታ ሥራ መሥራት ይቻላል፡፡ ዲያስፖራዎች ሀብትና እውቀታቸውን አሰባስበው ሆስፒታል በአዲስ አበባም የከፈቱ አሉ፡፡ ይህንን መሰል ሥራ ለማከናወን የጤና ዲፕሎማሲ ሥራ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

### ዓለም አቀፍ የጤና ኮንፍረንሶችን ለማከናወን

የጤና ዲፕሎማሲ ተግባር ውስጥ አንዱ የሆነው በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ዓለም አቀፍ ኮንፍረንሶችን በሀገራችን እንዲከናወን የሎቢ(Lobby) ሥራ መሥራት ነው፡፡ ይህ ተግባር ስለጤና የሚከናወነው ኮንፍረንስ ከሚሰጠው እውቀት በተጨማሪ የኮንፍረንስ ቱሪዝም ለማከናወንም ያግዛል፡፡ የሀገራችንም የህክምና ባለሙያዎች የጥናትና ምርምር ውጤቶቻቸውን የሚያቀርቡበትን እድል ይፈጥራል፡፡ በተመሳሳይ ዓለም አቀፍ ኮንፍረንሶች በውጭ ሀገር ሲከናወኑ የሀገራችን ምሁራን የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በጤና ዲፕሎማሲ አማካኝነት ድጋፍ እንዲኖር ያስችላል፡፡

### የምርምር ውጤቶች በታዋቂ ጆርናሎች እንዲታተሙ ማገዝ

የጤና ሥራ እና ምርምር በእጅጉ የተያያዙ ናቸው፡፡ የሀገራችን የህክምና ዶክተሮችና ባለሙያዎች የሚፅፏቸው የምርምር ውጤቶች በውጭ ሀገር ታዋቂ ጆርናሎች ላይ ሲታተሙ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህንን መሰል የምርምር ሕትመቶች እንዲወጡ የዲፕሎማቶች ድጋፍ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለያዩ ሀገራት ተመድበው የሚሰሩ ዲፕሎማቶች የትኛው ጆርናል ስመጥርና ተነባቢ ነው የሚለውን መረጃ በቀላሉ ማግኘት ስለሚችሉ የሀገር ውስጥ የህክምና ባለሙያዎችን ሊያግዙ ይችላሉ፡፡

### የሌሎችን ሀገሮች ፖሊሲ ለመረዳትና ለመጠቀም

የጤና ዲፕሎማሲ ሥራ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ የሌሎች ወሳኝ ሀገራትና አህጉራትን የጤና ፖሊሲ የመረዳትና ከዚያ ፖሊሲ በመነሳት የሀገር ጥቅምን ማፈላለግ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የአውሮፓ ህብረት የዓለም አቀፍ የጤና ስትራቴጂ(European Union Global Health Strategy) አለው፡፡ በተመሳሳይም አሜሪካና ሌሎች ኃያላን ሀገራት ይህንን መሰል ስትራቴጂዎች አሏቸው፡፡ ቻይናም ተመሳሳይ የጤና ስትራቴጂ (Health Silk Road) አላት፡፡ እነዚህ ስትራቴጂዎች ሲተገበሩ ለሀገራችን ሊያበረክቱ የሚችሉት ጥቅም ምን እንደሆነ በማጥናትና በዲፕሎማሲ ጥበብ በመታገዝ ብሔራዊ ጥቅም ላይ መሥራት ያስችላል፡፡

### የሀገራችን የመድኃኒት ፋብሪካ ገበያ ማፈላለግ

በሀገራችን የተለያዩ የመድኃኒት ፋብሪካዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ጥቂት ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸው መድኃኒቶች ከሀገር ፍላጎት በላይ ሲሆኑ የውጭ ገበያ የሚያስፈልጋቸው በመሆናቸው የጤና ዲፕሎማሲ ሥራ ይህንን ተግባር በማከናወን ፋብሪካዎች እየተጠናከሩና እየተስፋፉ እንዲሄዱ ያስችላል፡፡ ልክ ለቡና እና ለቅባት እህሎች ምርቶቻችን ዲፕሎማቶች ገበያ እንደሚያፈላልጉ ሁሉ ለመድኃኒት ምርቶቻችንም ገበያ ማፈላለግ ያስችላል።

### የጤና ምርምር ተቋማትን የማገናኘት

የጤና ጉዳይ ዓለም አቀፋዊ ጉዳይ በመሆኑ የተለያዩ ሀገራት ከጤና ጋር የተያያዙ የጥናትና ምርምር ተቋማትን የማቋቋም ሥራ ያከናውናሉ፡፡ በእኛም ሀገር የጤና የምርምር ተቋማት የሚገኙ ሲሆን ውጪ ከሚገኙ መሰል ተቋማት ጋር በጋራ እንዲሰሩ ለማስቻል የጤና ዲፕሎማሲ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የምርምር ተቋማት በጋራ ጥናትና ምርምር እንዲያከናውኑ፣ ተሞክሮ እንዲቀያየሩ፣ የውይይት መድረክ በጋራ እንዲያዘጋጁ፣ ሥልጠናዎችን አንዱ ለአንዱ እንዲሰጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎችን ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

ለማጠቃለል ያክል የጤና ዲፕሎማሲ ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ለሀገራችን እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ ሥራ ፍጹም ያልተሰራ ነው ለማለት ሳይሆን አስፍቶና አጠናክሮ መሥራት ወቅቱ የሚጠይቀው ነው ለማለት ነው፡፡ ይህን ተግባር በተለያዩ የአሰራር ሥርዓት ሊተገበር ይችላል፡፡ አንዳንድ ሀገሮች የወታደር፣ የባሕል፣ የጤና አታሼ በኤምባሲዎች በመመደብ በየዘርፉ የዲፕሎማሲ ሥራ ያከናውናሉ፡፡ እኛም በተመረጡ ጥቂት ሀገሮች ውስጥ የጤና አታሼ እንዲመደቡ ወይም የጤና ትምህርት ያላቸው ዲፕሎማቶች በዘርፉ ላይ ተመድበው እንዲሰሩ ማድረጉ ጠቃሚ መሆኑን የግል አስተያየቴን እያቀረብኩ ጽሑፌን በዚሁ እቋጫለሁ፡፡

# ስፖርት





# ‹‹የእግር ኳስ ሥልጠና መንገዳችን መመርመር ይኖርበታል››


## -አሠልጣኝ ገብረመድኅን ኃይሌ

ዓለማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለ2025ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ በቅርቡ ባደረጋቸው ሁለት ጨዋታዎች አንድ ነጥብ ብቻ ማግኘቱ ይታወሳል፡፡ ቡድኑ ውጤት ለማጣቱ የሥልጠና መንገዶች፣ ከሜዳ ውጪ መጫወት፣ ከጉዳትና ከሌሎች ችግሮች ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ተፅዕኖ መፍጠራቸውን አሠልጣኝ ገብረመድኅን ኃይሌ ተናግረዋል፡፡ የዋሊያዎቹ አሠልጣኝ ገብረመድኅን ኃይሌ ቡድናቸው ከታንዛኒያ እና ዲሞክራቲክ ኮንጎ ጋር ያደረጋቸውን ጨዋታዎች አስመልክተው ከትናንት በስቲያ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የመጀመሪያውን እና ሁለተኛውን የምድብ ማጣሪያ ጨዋታዎቹን አከናውኖ በአንዱም ግብ ማስቆጠርና ማሸነፍ ሳይችል መቅረቱ ይታወቃል፡፡ ቡድኑ ከታንዛኒያ ጋር ያለምንም ግብ ሲለያይ በዲሞክራቲክ ኮንጎ 2ለ0 ተሸንፏል፡፡ ቡድኑ በአፍሪካ ዋንጫና በሌሎች የነጥብ ጨዋታዎች ማሸነፍ እየተሳነው መምጣቱ የሥልጠና መንገዶች፣ ከሜዳ ውጪ መጫወት፣ ከጉዳትና ከሌሎች ጉዳዮች ጋር የተገናኙ ችግሮች ምክንያት መሆናቸውን አሠልጣኙ አስረድተዋል።

አሠልጣኙ ከታንዛኒያ ብሔራዊ ቡድን ጋር የተደረገው የመጀመሪያው ጨዋታ ጥሩ ቢሆንም በዋልያዎቹ የአጥቂ ስፍራ ላይ ትልቅ ችግር መኖሩን ጠቅሰዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ብዙ የመስመር እና የፊት አጥቂዎች ከጤና እንዲሁም ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ቡድኑ ውስጥ አለመካተታቸውን አንስተዋል፡፡ በሁለተኛው ጨዋታ ዲሞክራቲክ ኮንጎ በአፍሪካና በዓለም እግር ኳስ ደረጃ ከፍተኛና ተጫዋቾቻቸውም በትልቅ ደረጃ የሚጫወቱ በመሆኑ ያገኙትን አጋጣሚ ተጠቅመዋል ብለዋል፡፡




እንደ አሠልጣኙ ማብራሪያ፣ ቡድኑ የአጨራረስ ችግር ቢኖርበትም ተጭኖ ለመጫወትና ኳስ ለመቀማት የሚያደርገው ጥረት ጥሩ ነው፡፡ ሁለቱም ብሔራዊ ቡድኖች በዓለም እግር ኳስ ደረጃ በ30 እና በ83 ደረጃዎች መብለጣቸው ትልቅ ልዩነት መኖሩን ማሳያ ነው፡፡ ብሔራዊ ቡድኑ በስደት ጨዋታዎች ጎል ማግባት ያልቻለው ብዙ ዕድሎችን መጠቀም ሳይችል ቀርተው እንጂ ቡድኑ መጥፎ በመሆኑ አይደለም፡፡

ለዚህም ኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግና ብሔራዊ ቡድን ሁነኛ ዘጠኝ ቁጥር አጥቂ እንደሌለና የውጪ ሀገር ዜጎች ኮከብ ግብ አግቢ መሆናቸው የዚሁ ማሳያ መሆኑን አሠልጣኙ ጠቅሰዋል፡፡ የአጥቂ ችግሩን ለመፍታት የረጅም ጊዜ እቅድ በመያዝ ከስር መሠረቱ ሊሠራ ይገባል ያሉት አሠልጣኝ ገብረመድኅን፣ የሥልጠና መንገዱም መመርመርና ትክክለኛ መንገድ የሚከተልበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል ባይ ናቸው፡፡ የእግር ኳስ ፕሮጀክቶች ላይ አብዛኛውን ጊዜ ኳስን ማንሸራሸር ላይ ብቻ የተመሠረተ ሥልጠና እንደሚሰጥ በመጠቆም፣ ፕሪሚየርሊጉ ላይ ብዙ ግቦች የማይቆጠሩትም በዚሁ ምክንያት ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ወጣቶች ላይ ቶሎ ቶሎ ወደ ግብ የመድረስና የማስቆጠር ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት ይኖርበታል፡፡›› ያሉት አሠልጣኙ፣ አጥቂ በብሔራዊ ቡድን ደረጃ የሚፈጠር እንዳልሆነና ከመጀመሪያውም ለቦታው የሚሆን ተፈጥሯዊ ክህሎት ይዞ መገኘት እንደሚኖርበት ጠቅሰዋል፡፡ አብዛኛዎቹን በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ኮከብ ግብ አግቢ ሆነው የሚያጠናቅቁ የአጥቂ ስፍራ ተጫዋቾችን ማብቃታቸውን የገለጹት አሠልጣኙ አጥቂ ለማብቃት ረጅም ጊዜ ተወስዶ የሚሠራ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

በሁለቱም ጨዋታዎች የቡድኑ አቋም የወረደው ብሔራዊ ቡድኑ የተሰባሰበው ውድድር በማይካሄድበት ወቅት በመሆኑ ተጫዋቾች እረፍት ላይ መሆናቸው የአካል ብቃት፣ ክብደት መጨመር እና ከጉዳት ጋር የቅንጅት ሥራዎችን ለመሥራት ጊዜ እንደወሰደ ተናግረዋል። በአጭር ጊዜ የተጫዋቾቹን ብቃት በማስተካከል እና ተጭኖ ተጫውቶ አራት ነጥቦችን ለማሳካት አቅደው እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ይሁንና ከሜዳ ውጪ እየተጫወቱ ውጤት ማምጣት አስቸጋሪ ነው የሚሉት አሠልጣኝ ገብረመድኅን፤ ለብሔራዊ ቡድኑ ውጤታማነት ችግሮቹ ምን እና የት እንደሆኑ በዝርዝር ለማወቅ ብዙ ጥናቶች መደረግ እንደሚኖርባቸው ጠቁመዋል፡፡ በሜዳና ደጋፊዎች ፊት የመጫወት ዕድል አለመኖሩ እግር ኳሱን በብዙ መልኩ ጎድቶታል፡፡ በሚያውቁት አየር፣ በደጋፊ እና ከተፅዕኖ ነፃ ሆኖ የመጫወት ለውጤታማነት የሚያበቃ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ ይገባል። በሜዳ ማሸነፍ በብሔራዊ ደረጃ በሊጉና በሀገር ደረጃ የመነሳሳት ኃይል ስለሚፈጥር ብሔራዊ ቡድኑ እንዲያሸነፍ ለሜዳ ተጠቃሚነት ትኩረት መሰጠት ይኖርበታል፡፡

ለሀገር መሥራት የሚያስደስት ቢሆንም ውጤት ባለመሳካቱ በክለብ ሆነ ብሔራዊ ቡድን መሥራት ሰልችቶኛል በማለትም ተናግረዋል፡፡ አሠልጣኙ አክለው እንደገለፁትም፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ተጫዋቾች አሁን የሚገኙበት አቋም ጥሩ ደረጃ ነው ማለት አይቻልም። ብሔራዊ ቡድኑ ከሚገጥሙት ሽንፈቶች ጎን ለጎን ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ቢሆንም ውጤታማ እንዳልሆነና ብዙ መሥራት እንዳለበት ያሳያል፡፡ ተጫዋቾች የአንድና ሁለት ጨዋታ ኮከቦች ብቻ በመሆናቸው በመገናኛ ብዙኃን ሊተቹና ሊመከሩ እንደሚገባ አሠልጣኝ ገብረመድን ጠቁመዋል፡፡